

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/



ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ የ2015 ዓ.ም. መጀመሪያ ስብስብ

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ)

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 221483

ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ሰናይት አድነው

ደጀኔ አያንሳ

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ መንግስቱ ታይለማርም
2ኛ. አቶ ፈቃዱ ታይለማርም
3ኛ. አቶ ፍቅሩ ታይለማርም
4ኛ. ወ/ሮ ሰናይት ታይለማርም
5ኛ. አቶ ብርሃኑ ታይለማርም
— ጠበቃ ታደሰ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሪት ሜሮን ሰይፈ ታይለማርም
2ኛ. ወ/ሪት ናርዶስ ሰይፈ ታይለማርም
3ኛ. አቶ ያፌት ሰይፈ ታይለማርም
4ኛ. አቶ አልአዛር ሰይፈ ታይለማርም
— 4ኛ ተጠሪ በራሳቸውና ስለሌሎቹም ቀረቡ
5ኛ. አቶ አበራ ፈለቀ አበራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

6ኛ. አቶ ሚካኤል ፈለቀ አበራ

7ኛ. ወ/ሪት ቤተልሄም ፈለቀ አበራ አልቀረቡም

8ኛ. አቶ ኤፍሬም ፈለቀ አበራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 15/06/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 200709 በቀን 29/03/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ።

ከሳሾች በቀን 02/06/2010 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከተ/ቁ 1ኛ-4ኛ የተዘረዘሩት ተከሳሾች የሟች ወንድማችን ልጆች እንደዚሁም ከተ/ቁ 5ኛ-8ኛ የተዘረዘሩት ተከሳሾች የሟች እህታችን ልጆች ናቸው፤ የሟች አባታችን አቶ ኃ/ማርያም ሀብተወልድና የሟች እናታችን ወ/ሮ የሺ ሀብተማርያም የውርስ ሀብት ተጣርቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርቦ የወራሽነት ማስረጃ ተሰጥቶናል፤ ሟቾቹ አባትና እናታችን በህይወት ዘመናቸው ያፈሩት በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቤ/ቁ 329 እና 363 የሆኑ ቤቶች ያሏቸው መሆኑ ተረጋግጦ የእነ ኃ/ማርያም ሀብተወልድ ወራሾች የሚል የነባር ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶናል፤ ይሁን እንጂ ተከሳሾች ቤቶቹን በመያዛቸው የድርሻ ክፍፍል እንድናደርግ በተደጋጋሚ ብንጠይቃቸውም ፈቃደኛ አልሆኑም። ስለዚህ ተከሳሾች ቤቶቹን ለቀው በስምምነት ወይም በጨረታ ተሸጠው በድርሻችን መጠን እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የስር ተከሳሾችም በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አስቀድመው ከሳሾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት በ27/09/2001 ዓ.ም አባታቸው ከሞቱ ከ 41 ዓመታት እናታቸው ከሞቱ ከ 27 ዓመታት በኃላ በመሆኑ እና ክስ የቀረበባቸው ንብረቶች ከ 20 ዓመታት በላይ በተከሳሾች እጅ የሚገኝ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) እና (2) እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች መሰረት ክሱ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብለዋል። በፍሬ ነገር መልሳቸው ቤቶቹ በተከሳሾች ለ20 አመትና ከዚያ በላይ የተያዙ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት እያሳደስን ቆይተናል፤ የውርስ ሀብት ያልተጣራ ሲሆን እነ በሚል በወራሾች ስም አልተዛወረም፤ የቤ.ቁ 363 ካርታው ወ/ሮ የሺ ኃ/ማርያም የሚል ነው፤ ከሳሾች ክስ ያቀረቡባቸው ቤቶች የውርስ ሀብቱ ያልተለየባቸውና በተ/ቁ 2 የተጠቀሰው ቤት ከሳሾች ባቀረቡት የወራሽነት ማረጋገጫ ውስጥ የሌለ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በድጋሚ እንዲያጣራልን በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ከሳሾች ያቀረቡት ክስ የውርስ ንብረት ክፍፍል እንጂ የውርስ ማጣራት ጥያቄ አይደለም፤ የውርስ ክፍፍል ጥያቄ ደግሞ ውርሱ ከተጣራ በኃላ በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ስለሆነ ተከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል። በፍሬ ጉዳዩ ላይም ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የውርስ ሀብት መሆናቸውና ከሳሾች የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ህ/ቁ 842(1) እና (2)፣ 1086 እና ተከታዬቹ መሰረት ተከሳሾችን ጨምሮ ድርሻቸውን ተካፍለው ሊወስዱ ይገባል፤ ተከሳሾች ቤቱን ለመጠገኛ ያወጡት ወጪ ካለ መጠኑን ገልጸው ሌላ ዳኝነት መጠየቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ተከሳሾች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ከሳሾች ወራሽነታቸውን እና ውርሱን በህጉ ግዜ ገደብ ውስጥ ሳያረጋግጡ የስር ፍ/ቤት ተከሳሾች ያነሱትን የይርጋ መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤ የስር ከሳሾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔን ሽሮታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የአመልካቾችና የተጠሪዎች የውርስ ሀብት በመ/ቁ 2056/2001 ተጣርቶ የቀረበ ስለመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት አረጋግጧል፤ በውርስ ማጣራት ሂደቱ አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪዎች የተካተቱበት ሲሆን አመልካቾች የሚች ወላጆቻችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ስለመሆናችን በውርስ ማጣራት ሂደቱ የተረጋገጠ ሲሆን በተጠሪዎች የተካደ ጉዳይ አይደለም፤ ከዚህም ባሻገር አመልካቾች ወራሽነታችንን በህጉ አግባብ ያረጋገጥን ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል። ውርስ ተጣርቶ በቀረበ ንብረት የሚጠየቅ የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ላይ የይርጋ ህግ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም። ውርስ በተጣራ ግዜ በማናቸውም ግዜ ቢሆን የውርስ ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1062 መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡበትን ግዜ ብቻ ግምት በመውሰድ በውርሱ ስለመጣራቱ ከዚህ አኳያ

የይርጋ ድንጋጌ የተፈጻሚነት ወሰን ምን እንደሆነ ሳይመለከት ውሳኔ ላይ መድረሱ ህግን ያልተከተለ በመሆኑ ሰበር ሰሚው ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ወሳኔውን እንዲያርምልን፡፡ ክርክር የተነሳባቸው ቤቶች በተጠሪዎች ስም ያልተዛወረ እና ተጠሪዎች እነዚህ የውርስ ሀብቶች ስላለመሆናቸው ወይም አመልካቾች የማይመለከታቸው ስለመሆኑ ምንም አይነት ተቃራኒ ማስረጃ አለማቅረባቸው በከፍተኛው ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ክርክር የቀረበባቸው የውርስ ሀብት የሆኑት የቤ/ቁ 329 እና 363 ቤቶች የአመልካቾችና ተጠሪዎች የጋራ የውርስ ሀብት መሆናቸውን ጭምር ከከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተጣርቶ በቀረበ የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ የይርጋ መከራከሪያ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑ በግልጽ እየታወቀ የውርስ ሀብት በአመልካቾች እና ተጠሪዎች በጋራ ተጣርቶ የቀረበ መሆኑን ወደ ጎን በማለት የአመልካቾችን ወራሽነት ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ የአመልካቾችን ጥያቄ በይርጋ ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የጠቅላይ ፍ/ቤት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ውርስ ሲጣራ የተጠሪዎች ወላጆች መኖራቸውና በወቅቱም ተቃውሞ ስለማቅረባቸው ያልተጣራ ወይም ክርክር ያልቀረበ ከመሆኑ አኳያ አሁን የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል የተባለበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ አመልካቾች በአቤቱታቸው ላይ በተደጋጋሚ ግዜ የሟች አባታችን አቶ ኃ/ማርያም ሀብተወልድ እና የሟች እናታችን ወ/ሮ የሺ ሀብተማርያም የውርስ ሀብት አመልካቾችንና ተጠሪዎችን አካቶ ተጣርቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርቦ የወራሽነት ማስረጃ ተሰጥቶናል በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ አመልካቾች ወራሽነታችን ይረጋገጥልን በሚል አቤቱታ ያቀረቡት በቀን 15/08/2001 ዓ.ም ሲሆን በ27/09/01 ዓ.ም የተጻፈ ውርስ ያጣራንበት ሪፖርት ነው በሚል ደግሞ ራሳቸው አጣርተናል በሚል በመዝገቡ ውስጥ አያይዘዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ግን አመልካቾች የሟቾች ወራሽነታቸው ተረጋግጧል በሚል ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡን ዘግቶ ተመላሽ አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን አመልካቾች በምን የህግ አግባብ እንደሆነ በማይታወቅ እና መልካም አስተዳደር በጎደለው ሁኔታ ከፍ/ቤቱ ውሳኔ ከተሰጠበት 12 ቀን በኋላ በእጅ የተጻፈ የውርስ ማጣራቱ ለማስረጃነት ይሰጥ በሚል ከውሳኔው መጨረሻ ተጽፎ ከመገኘቱ ባለፈ ተጠሪዎች በጋራ ያጣራነው እና ያቀረብነው የውርስ ማጣራት ሪፖርት

እንዲጣራልን ውሳኔ ከሰጠው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት መዝገቡ ቀርቦ እንዲታይልንና አስተያየት እንድንሰጥበት አመልክተን የስር ፍ/ቤት ግን መዝገቡን ካስመጣ በኋላ ሲመለከተው ቀድሞውኑ የውርስ አቤቱታውን በዚሁ አዲስ አበባ ፍ/ቤት ያዩት ዳኛ በመሆናቸው ቢችሉ ቀድሞ በስር ፍ/ቤት ያየሁት ጉዳይ ነው በማለት ጉዳዩ በሌላ ችሎት እንዲታይ ትእዛዝ ሊሰጡበት ሲገባ ይህን አልፈው እንዲጣራልን የጠየቅነውን አቤቱታ እና መዝገቡ ከመጣ በኋላም አስተያየት እንድንሰጥበት የጠየቅነውን አቤቱታ በምን አግባብ እንኳ እንደታለፈ ሳይገለጽልን ውሳኔ ተሰጥቷል እንጂ አመልካቾች እንደሚሉት ተጠሪዎችን በማሳተፍ የተከናወነ የውርስ ማጣራት የለም። የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ እውነታ የሚያሳየውን ማስረጃ በሚገባ ተመልክቶ በተደረገው ተገቢ ያልሆነ ተግባር እርምጃ መውሰድ እየቻለ ይህን አልፎ የቀረበለት ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሮ ውሳኔ ላይ መድረሱ ሊያስመሰግነው ሲገባ ዛሬም ይህን እውነታ ደብቀው በሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ አይመዝንም ከሚል መንፈስ ያቀረቡት አቤቱታ መሆኑን ችሎቱ ተረድቶልንና ከእኛ ተጠሪዎች ጋር በጋራ ያጣራነው የውርስ ሀብት አለመኖሩን ተረድቶልን በአመልካቾች በተደጋጋሚ ግዜ በጋራ ውርሱ ተጣርቶ ቀርቧል በሚል የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ። አመልካቾች ውርስ በህግ አግባብ አላጣሩም እንጂ ተጣርቷል ቢባል እንኳን የወራሽነት አቤቱታ ያቀረቡት የይርጋ ጊዜው ካለፈ በኃላ በመሆኑና የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ለመጠየቅ ብቻም ሳይሆን መብቱንና የውርስ ንብረቱ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከ3 አመት በኋላ የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በራሱ በህግ ባጡት መብት ላይ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነው የፌ/ከፍተኛ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፈው ብይን፤ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ክርክሩንና ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም በአመልካቾች ለስር ለፍርድ ቤት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ይዘት በአግባቡ ተለይቶ ጉዳዩን በህጉ በተዘረጋው ስርዓት በመምራት ውሳኔ የተሰጠበት ስለመሆን አለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል።

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ብይን የሰጠው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1062 ላይ ውርስ በተጣራ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ወራሾች ውርሱን ለመከፋፈል ለመጠየቅ እንደሚችሉ ተደንግጓል በሚል ነው። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ደግሞ አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ነው ያለው ከሳሾች ወራሽነታቸውን እና ውርሱን በህጉ ግዜ ገደብ ውስጥ አላረጋገጡም በሚል ነው።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሠ) እና 245 ስር እንደተደነገገው ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ እንደሚሰጥ፤ በመጨረሻም የቀረበው መቃወሚያ ከክሱ ይዘትና ከማስረጃው አንፃር ተመርምሮ መቃወሚያው ተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑን/አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ መርምሮ ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን/ትዕዛዝ ይሰጣል።

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነው ግራቀኙ በመቃወሚያው ላይ ያደረጉት ዝርዝር ክርክር የነበረ ስለመሆኑ በመዝገቡ ተመልክቶ ነገር ግን በመቅረፀ ድምፅ የተሰማው የግራ ቀኙ ክርክር በቫይረስ ምክንያት ጠፍቷል በመባሉ የመዝገቡ አካል አልተደረገም። መቃወሚያውን ለመወሰን እንዲረዳም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የመ/ቁ 2050/01 የሆነው መዝገብ እንዲቀርብ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንደነበር መዝገቡ ያሳያል። ይሁንና ይቅረብ የተባለው መዝገብ ይዘት ከተጠየቀው ዳኝነት እና ከግራቀኙ የመቃወሚያ ክርክር ጋር ስለመመርመሩ ምንም ሳይባል ከፍሏል የተጠቀሰው ብይን ተሰጥቷል።

መቃወሚያውን ከክሱ ይዘት ጋር አያይዞ በመመርመርና በአግባቡ በማጣራት፤ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች እኩል ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ እድል በመስጠት፤ እንዲሁም ለብይኑ አሰጣጥ ይረዳል ተብሎ ትዕዛዝ የተሰጠበትን መዝገብ ይዘትም ከክርክሩ አንጻር ታይቶ ብይኑ ሊሰጥ ይገባ ነበር። ይሁንና የስር ፍርድ ቤት በዝርዝር ጉዳዩን አጣርቶ በህጉ አግባብ ብይን ሊሰጥበት ሲገባ በዚህ አግባብ አይቶ አለመወሰኑን ተረድተናል። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከዚህ አንጻር ሳይመለከት መወሰኑ የሚነቀፍ ነው።

በአጠቃላይ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ይዘት በአግባቡ ሳይጤን እና ግራ ቀኙን የሚያለያያቸው የመቃወሚያ ክርክር ተገቢው ትጋት ተደርጎበት በማስረጃ በአግባቡ እንዲጣራ ሳይደረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተላለፈው ብይንና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0129743210205 በቀን 20/05/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ብይንና በቀን 29/10/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 200709 በቀን 29/03/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል።

2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች እኩል የመከራከርና ማስረጃ የማቅረብ እድል በመስጠት፤ መቃወሚያውን ለመወሰን ይረዳል በሚል እንዲቀርብ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የመ/ቁ 2050/01 የሆነ መዝገብ ይዘት በመመርመር በመቃወሚያው ላይ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 341/1/ እና 245 መሰረት መልሰናል። የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

3. ከፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ።

4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

??/? /?? ? 221177
?? 4/2/2015?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)
ቀነዓ ቂጣታ
ፈይሳ ወርቁ
ደጀኔ አያንሳ
ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - 1. አቶ ኪያር ኢብራሂም
2. አቶ ሙስጠፋ ኢብራሂም
3. ወ/ሮ ዙበይዳ ኢብራሂም
4. አቶ አብዱልጀዋድ ኢብራሂም
5. ወ/ሮ አሻ አብዶ
} ጠበቃ አሸማዊ ሰይፉ ቀረቡ

ተጠሪ - ወ/ሮ አማኔ ሁሴን ፡- የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካቾች የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 392628 ጥር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 381061 ጥር 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ ቅሬታቸውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካቾች የሚቃወሙባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚሉትን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሟች ያደረገው ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም ተብሎ ፈራሽ ተደርጎ እያለ፣ የስር ፍ/ቤቶች በሻሻመኔ ከተማ ውስጥ ያለውን ቤት በተመለከተ ኑዛዜውን መሰረት በማድረግ ከኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 74 ትርጉም ውጪ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት እዳ አለው ተብሎ ባለመብቱ ሳይጠይቅ የብር 1,200,000 በጋራ ይክፈሉ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያለነው ከሳሾች የሚች ወራሾች ስንሆን 5ኛ ከሳሽ የሚች ባለቤት ነች፡፡ የሚች የውርስ ንብረት በባሌ ዞን በአጋርፋ ከተማ፣ በሻሻመኔ ከተማ፣ በአዳባ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወረዳ፣ በአዳማ ከተማ እና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንደሚገኝ ጠቅሰው ድርሻችንን ታካፍለን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን ተጠሪ በአ/አበባ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት በ171 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ሲሆን እኔና ሟች ባለቤቱ ያፈራነው ንብረት ነው፡፡ ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ልጆቻችንን የማሳድግበት ነው፡፡ ይህን ቤት ከሰው ብር 1,200,000 ተበድረን የገዛነውና እዳው ያልተከፈለ ነው፡፡ ሟች በ16/12/2008 ዓ/ም ባደረገው ኑዛዜ ይህን ቤት ተናዞልኛል፡፡ በአዳማ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት ተሸጧል፡፡ ቀሪውን ብር 100,000 1ኛ ከሳሽ ተቀብሏል፡፡ ለኔም ድርሻዬን ይስጠኝ፡፡ በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት የውርስ ንብረት ሳይሆን እኔ አረብ ሀገር ሰርቼ ያፈራሁት የግል ንብረቴ ሲሆን ሟችም በኑዛዜው ላይ የኔ ስለመሆኑ አውቆልኛል፡፡ በምዕራብ አርሲ ዞን በአዳባ ወረዳ ለጆ ብርብሪሳ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በተራ ቁጥር 4ኛ ላይ የተጠቀሰው ቤት የሟች እናት የወ/ሮ አሻ ዋዶ ንብረት ነው፡፡ በምዕራብ አርሲ ዞን በአዳባ ወረዳ ለጆ ብርብሪሳ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በተራ ቁጥር 5ኛ ላይ የተጠቀሰው ቤት እና በአጋርፋ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤት ለ5ኛ ከሳሽ ለወ/ሮ አሻ አብዶ እና ለልጆቿ በኑዛዜ የተሰጣቸው ነው፡፡ በባንክ ገንዘብ ስለመኖሩ አላውቅም፡፡ ካለ ተጣርቶ እንካፈል፡፡ በአዳባ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ሟች ለሁላችንም በኑዛዜ አከፋፍሎናል፡፡ 1ኛ ከሳሽ ሟች መድሀኒት ከለከለኝ በሚል ከውርስ የነቀለው በመሆኑ የውርስ ንብረት ሊጠይቀኝ አይችልም በሚል መልስ ሰጥታለች፡፡

የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 32150 ጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችለት በሰጠው ውሳኔ የተሰሙትን ምስክሮች እና የጽሁፍ ማስረጃ እንደመረመርነው ሟች ኑዛዜ ያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የኑዛዜው ህጋዊነት ስናይ፣ ሟች ሁለት ሚስቶች ያሉትና ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር በጋራ ባፈራቸው ንብረቶች ላይ የሰጠው ኑዛዜ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ 1ኛ ከሳሽ ከውርስ የተፈናቀለበት ምክንያት ሲታይ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 938 ድንጋጌ አንጻር ሟች 1ኛ ከሳሽ ከውርስ የነቀለው ከሐኪም ቤት የተሰጠውን ትልቅ መድሃኒት ስለከለከለችና ምንም እገዛ ሳያደርግልኝ ጥሎኝ የሄደ፣ ሞቴንም አፋጥኗል በሚል ሲሆን ተናዛዥ ሊረዳኝ እና ሊያሳክመኝ ስላልቻለ በሚል ምክንያት ከውርስ መንቀል እንደማይቻል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57836 ቅፅ 11 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ 1ኛ ከሳሽ ካለ በቂ ምክንያት ከውርስ መነቀል ስለሌለበት ኑዛዜው ውድቅ ነው፡፡ በመሆኑም በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት ሟች እና ተከሳሽ በትዳር ውስጥ እያሉ የተፈራ ንብረት መሆኑ በመረጋገጡ ተከሳሽ የግሌ ነው የምትለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት የሶስቱም የጋራ ንብረት ሲሆን እዳ አለበት የተባለው፣ እዳ ያለበት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አዳማ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት መሸጡ የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪውን 100,000 ብር 1ኛ ከሳሽ ያልወሰደ ስላለመሆኑ አላስተባበለም፡፡ በመሆኑም ይህን ብር ሊመልስ ይገባል፡፡ በአጋርፋ ከተማ ውስጥ እና በአዳባ ወረዳ ቢርቢርሳ ከተማ ውስጥ የሚገኙት ቤቶች ተከሳሽን ከማግባቱ በፊት የተፈሩ ንብረቶች መሆኑ በመረጋገጡ ተከሳሽ መብቱ የላትም፡፡ በአዳባ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው የመሬት ይዞታ ሶስቱም ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ በመረጋገጡ የሶስቱም የጋራ ሀብት ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተከሳሽ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 381061 ጥር 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት በተመለከተ 3ኛ ወገን የብር 1,200,000 እዳ የሚጠይቅ ካለ ከሳሾች እና ተከሳሽ ባገኙት ድርሻ ልክ እዳ ለመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤት የተከሳሽ የግል ንብረት ስለመሆኑ የሰው ምስክሮች አረጋግጠው እያለ ሟች በኑዛዜው የግል ንብረቷ ስለመሆኑ ገልጻ እያለ የጋራ ንብረት ነው መባሉ ስህተት ነው፡፡ ይህ ቤት የተከሳሽ የግል ንብረት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ ከሳሾች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው በመ/ቁጥር 392628 ጥር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ አያስቀርብም ሲል አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ የግራ ቀኙን ክርክር በተመለከተ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች አድርጎታል የተባለውን ኑዛዜ በመሻር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አሁን ለሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ መነሻ የሆነውን በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በተጠሪ ስም ቢመዘገብም ጋብቻቸው ባለበት ጊዜ ውስጥ የተፈራ ንብረት በመሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት አይደለም በሚል ክርክሯን ውድቅ እድርጎ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 6 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ስትል ተከራክራለች፡፡ አመልካቾችም ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ቤቱ ተመዝግቦ ያለው በአሁን ተጠሪ ስም ሲሆን ተጠሪም አረብ ሀገር ሰርቼ ባገኘሁት የግል ገንዘቤ የተሰራ በመሆኑ የግል ንብረቴ ነው ስትል ተከራክራለች፡፡ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ከሟች ጋር በጋብቻ ውስጥ እያለ የተፈራ ንብረት በመሆኑ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን ይህ በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በተመለከተ የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲል ወስኗል፡፡ ሟች አድርጓል የተባለው ኑዛዜ በተመለከተ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሻረው ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያመልታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሟችም ባደረገው ኑዛዜ በተመለከተ ሟች ቤቱ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ ተቅሷል ከሚል በቀር ኑዛዜው ተፈጻሚ እንዲኖረው በማድረግ በኑዛዜው መሰረት የአሁን ተጠሪ ንብረት ነው በሚል ስለመወሰኑ አያመልክትም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሻሻማኔ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲል የወሰነው በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስራጃዎች መዝኖ ስለመሆኑ የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1) መሰረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙ ሲረጋገጥ ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ በመሆኑም አመልካች የከፍተኛ ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሻሩ ተገቢ አይደለም የሚል የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ቅሬታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች በክርክሩ የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን ውሳኔ የሰጡ ሲሆን ለዚህ ችሎት ማሰረጃ የመመዘን ሥልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ የአሁን አመልካች ቅሬታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝና ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 392628 ጥር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 381061 ጥር 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 221097

ጥቅምት 1 ቀን 2015የሰበር መዝገብ

ቁጥር 221097 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሙሉጌታ ዘውዱ፡- ከጠበቃ ሲሳይ ወርቅነህ ጋር ቀርቧል

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሄለን ደረሰ፡- ከጠበቃ የኃላወርቅ ተከተለው ጋር ቀርቧል

2ኛ. ወ/ሮ ፍቅርተ ደረሰ፡- ጠበቃ መስፍን ጫኔ ቀርቧል

3ኛ. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅ/ጽ/ቤት

4ኛ. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት } አልቀረቡም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

አከራካሪው ሱቅ በሥጦታ የተገኘ ሳይሆን ከ4ኛ ተጠሪ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በኪራይ ያገኙት ሆኖአያለ ፤ የስጦታ ውል ተብሎ የቀረበው ሰነድም በቤቱ ማኅደር ውስጥ የሌለ ፤ ውሉም በሕግ የተመለከተውን ፎርም የማያሟላ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት ያልተደረገ በተንኮል የተዘጋጀ የመንደር ውል በመሆኑ ዋጋ የሌለው መሆኑን ፤ ዋጋ አለው ቢባል እንኳን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የባልና ሚስት የጋራ በሆነ ንብረት ላይ 1ኛ ተጠሪ ለብቻቸው ያደረጉት የስጦታ ውሉ የማይፀና መሆኑና የስጦታ ውሉም ለ1ኛ ተጠሪ በግል የተደረገላቸው መሆኑን ስለማይገልጽ በሕጉ የጋራ ንብረት እንደሆነ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይገመታል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር በጭብጥነት ሳይመረመር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 63 እና የሕገ - መንግስቱን አንቀጽ 34(1) የሚቃረንና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት ያወጡትን ያላገባ የምስክር ወረቀት በሀሰተኛ የቃለ - መሐላ አቤቱታ በማሳደስ የፈፀሙት ድርጊት ሕገ - ወጥነትን የሚያበረታታ መሆኑን ፤ የሥጦታ ውሉ በአራት ምስክሮች ፊት ባለመነበቡ ፤ ውሉን የፈረሙት ምስክሮችም ሁለት ብቻ በመሆናቸው እና ወ/ሮ ሃና ታደሰ የሥጦታ ውሉን በፈረሙበት ጊዜ በቤቱ ላይ መብት የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ሱቁ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ፤ 2ኛ ተጠሪም ጋብቻ የፈፀመችው እህታቸው የሆነችው 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ፈጽመማ እንደማታውቅ ያላገባ የምስክር ወረቀት አውጥታ ሱቁን ሲትሸጥላቸው የቅን ልቦና ገዥናቸው ተብው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መሻሩ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱም ውሳኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው አመልካች የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ፤ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን የመንግስት ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ በኪራይ የተገኘ ነው በማለት አመልካች ከሌሎች የባልና ሚስት ንብረቶች ጋር ያቀረቡትን የከፍፍል ጥያቄ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፍርድ ቤት አይደለም በማለቱ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ባቀረቡት ክስ ፤ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ቁጥሩ 249/124 የሆነው የቀበሌ ንግድ ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋር የተከራዩ ቢሆንም የግራቀኙ ጋብቻ ታህሳስ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ 3ኛ ተጠሪን በማሳሳት ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት በመውሰድ የጋራቸው የሆነውን የቀበሌ ንግድ ሱቅ ለ2ኛ ተጠሪ በሰነዶች እና ምዝገባ ጽ/ቤት በተደረገ የሽያጭ ውል ያስተላለፉ በመሆኑ ፤ 4ኛ ተጠሪ የኪራይ ውሉን እንዲሁም 3ኛ ተጠሪም ያለአግባብ የሰጠውን ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰርዝ አቤቱታ ቢያቀርቡም ባለመሰረዙ ፤ በተጭበረበረ መንገድ የወጣው ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሁም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ጋራ ንብረት ሽያጭ ውል ተሰርዞ 3ኛ ተጠሪ ሱቁን አካፍሎ ከአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል እንዲያደርግ ከወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪም በመልሳቸው አመልካች ያቀረቡት ክስ አስተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ፤ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ እና ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው በፍሬ ነገር ክርክራቸውም የቀበሌ ንግድ ቤቱ የወ/ሮ ሎሚናት ወ/ዓዲቅ የነበረ ሲሆን እሳቸው የ1ኛ ተጠሪ እህት ለነበሩት ወ/ሮ ሃና ታደሰ አስተላልፈው ከወ/ሮ ሃና ታደሰ በስጦታ ያገኙት የግል ንብረት በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ትዳር ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኃላ ያላገባ የምስክር ወረቀት አውጥተው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ሕጋዊ የሱቅ ሽያጭ ውል የሚፈርስበት

ምክንያት ባለመኖሩ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይይ ይዘት ያለው መቃወሚያን በማስቀድም በፍሬ ነገር መልሳቸው ሱቁን የገዙት 1ኛ ተጠሪ ትዳር የሌላት መሆኑ ተረጋግጦ በመሆኑ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው የሽያጭ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ትዳር ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከመፍረሱ በፊት 2ኛ ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በቃለ መሃላ የተደገፈ አቤቱታ አቅርበው ትዳራቸው ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም የወሰዱትን ምስክር ወረቀት እንዲመልሱ በደብዳቤ የተገለፀላቸው መሆኑ ፤ ክርክር ያስነሳው የቀበሌ ንግድ ቤት የኪራይ ውሉ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብቻ በመሆኑና ያላገባ የምስክር ወረቀት በማቅረባቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 መሠረት የተከራይነት መብቱ ለ2ኛ ተጠሪ የተላለፈ በመሆኑ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ የሰጡት አገልግሎት ባለመኖሩ እና ሥራቸውን በአግባቡ ስለሰሩ ልንከሰስ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ፤ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረምረው 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያለች የቀበሌ ንግድ ቤት በስጦታ ውል አግኝታ በትዳር ውስጥ እያለች የኪራይ ውል የተዋዋለች መሆኑ ፤ የግራቀኙ ትዳር ከመፍረሱ ስድስት ቀን አስቀድሞ ያላገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቃለ መሃላ አቤቱታ አቅርቧ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት የወሰደች መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ገልጾ ፤ 1ኛ ተጠሪ የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ስድስት ቀን አስቀድሞ ያላገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ አቅርባ ከሕግ ውጭ የወሰደችውን ያለገባ የምስክር ወረቀት በመጠቀም ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ሱቁን ማስተላለፏን ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ግንዛቤ መወሰዱን ግልፆ ፤ 3ኛ ተጠሪ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠው ያላገባ የምስክር ወረቀት ሕጉን ጠብቆ የተሰጠ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ፤ 1ኛ ተጠሪ የኪራይ ውሉን የተዋዋለችው በ2008 ዓ/ም ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያለች ሆኖ የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ትዳር የፈረሰው ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 40(1) መሠረት የአመልካችና 1ኛ ተጠሪ ትዳር ከፈረሰ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቁጥሩ 249/124 የሆነው የቀበሌ ንግድ ሱቅ ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ የሚካፈል በመሆኑ ከሕጉ ወጭ የሆነውን ያላገባ የምስክር ወረቀት መሠረት በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ህጋዊ ባለመሆኑ 4ኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን የቀበሌ ንግድ ቤት ለአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አካፍሎ የኪራይ ውል ሊይዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም 1ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩ የባልና ሚስቱ የጋራ ሳይሆን የግል ንብረታቸው ለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የንግድ መደብሩ የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም መባሉ ፤ 2ኛ ተጠሪ ሱቁን የገዙት በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረሱንና የሽያጭ ውሉ በተፈጸመበት ጊዜ ጋብቻ የሌላትና ያላገባ የምስክር ወረቀት ያወጣች መሆኑ እንዲሁም የንግድ መደብሩን 1ኛ ተጠሪ በግል ከእናቷ የተሰጣት መሆኑን በማረጋገጥ ከአንድ ጠንቃቃ እና ምክንያታዊ ገዥ የሚጠበቀውን ጥንቃቄ

በማድረግ በቅን ልቦና በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገው የመደብር ግዥ ውል እንዲፈረስ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተለያየ መዝገብ ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ አጣምሮ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለውሳኔ መሠረት ያደረገው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ክርክር የተነሳበት የቀበሌ ንግድ ቤት በ2008 ዓ/ም 1ኛ ተጠሪ የኪራይ ውል የተዋዋሉ በመሆኑ እና ትዳራቸውም የፈረሰው ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 40(1) መሠረት ትዳር በፍቺ ውሳኔ ሲፈርስ ቤቱ እንደሚከፋፈል ስለሚደነግግ በሚል ቢሆንም ፤ የንግድ መደብሩን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በውል ከ3ኛ ተጠሪ ያጉት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ እህት የሆኑት ወ/ሮ ሃና ታደሰ ሲጠቀሙበት ቆይተው 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ አመልካችን ሳይጨምር በግላቸው በስጦታ ያገኙ መሆኑን ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ የንግድ ድርጅት የስጦታ ውሉ እንደሚያመለክት እና አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የነበራቸው ትዳር ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል መደረጉን ገልፆ ፤ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የንግድ መደብሩ ያገኙ መሆኑን ባላስረዱበት የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ትዳር ከፈረሰ በኋላ የተደረገው የሽያጭ ውል ፈርሶ የንግድ ቤቱን እንዲካፈሉ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ አግባብ አለመሆኑን ፤ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በግል በስጦታ ያገኙት መደብር በትዳር ውስጥ ሆነውም ይሁን ከፍቺ በኋላ በግላቸው እንዳያስተላልፉ የሚከለክላቸው ሕጉ ካለመኖሩም በላይ የሽጭ ውሉ የሕግ ጥሰት የተፈፀመበት ነው ቢባል እንኳን 2ኛ ተጠሪ ካላቸው የዝምድና ቅርበት አኳያ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የጋብቻ ፍቺ ማድረጋቸውን ተረድተው ግዥ መፈፀማቸው አንድ ጠንቃቃ ገዥ መፈፀም ያለበትን ጥንቃቄ ማድረጋቸውን ያሳያል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አከራካሪው የንግድ መደብር ለ2ኛ ተጠሪ ከመተላለፉ በፊት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ወይንም የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ የቤቱን ማህዳር በማስቀረብ የመረመረው የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንግድ ቤት የቀድሞ ተከራይ ወ/ሮ ሎሚናት ወ/ዓዲቅ ወ/ጊዮርግስ መመሪያ ቁጥር 4/2009 ከመውጣቱ በፊት ቤቱን በሽያጭ ለወ/ሮ ሃና ታደሰ አስተላልፈው ከህዳር 4 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በወ/ሮ ሃና ታደሰ በስማቸው የኪራይ ውል ተዋውለው ቤቱን ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ/ም በተፃፈ የንግድ ስጦታ ውል የንግድ ቤቱ (መደብሩ) ለ1ኛ ተጠሪ ብቻ ተላልፎላቸው የኪራይ ውል ተዋውለው ቤቱን ይዘው ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ተላልፎ 4ኛ ተጠሪም በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው መመሪያ ቁጥር 4/2009 መሠረት የንግድ ቤቱን የኪራይ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ስም ወደ 2ኛ ተጠሪ ስም አዙሮ 2ኛ ተጠሪ እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ ፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተከራዩት ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ያገኙት የንግድ መደብር መሆኑን ፤ አመልካች የንግድ መደብሩን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያገኙ ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ባለመኖሩ የንግድ

መደብሩ ወደ 2ኛ ተጠሪ ከመተላለፉ በፊት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በመሆኑ ፤ 1ኛ ተጠሪ በግል በስጦታ ያገኙትን የንግድ መደብር በጋብቻ ውስጥ ሆነውም ይሁን ከፍቺ በኋላ በህጉ አግባብ በሽያጭ ማስለላፍን የማይከለክሉ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የሥር የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ሰሚው እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ ግራቀኙን እያከራከረ ያለው የንግድ ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ ከቀበሌ መከራየታቸው ፤ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ 3ኛ ተጠሪን በማሳሳት ያላገባ የምስክር ወረቀት ወስደው አከራካሪውን ሱቅ እህታቸው ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ማስተላለፋቸውን አረጋግጦ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እንዲከፋፈሉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች የመሻሩን አግባብነት መጣራት አለበት በማለቱ የፍርድ ቤቱ መጥሪ ለተጠሪዎች ድርሶ መልስ ሰጥተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በመልሳቸው አከራካሪውን የንግድ መደብር ከመንግስት የተከራዩት ሳይሆን በስጦታ ያገኙት የግል ሀብታቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ፤ ሱቁን (መደብሩን) ከቀበሌ ተከራይቷል የሚለው የአመልካች ክርክር በማስረጃ አለመረጋገጡን ፤ በወ/ሮ ሃና ታደሰ እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የስጦታ ውል በሕጉ የተመለከተውን ፎርማሊት የሚያሟላ ባለመሆኑ አይፀናም የሚለው የአመልከች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በመሆኑ በሰበር ደረጃ መነሳቱ ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ክርከሩ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በመሆኑና በንግድ መደብር ላይ የሚደረገው የስጦታ ውል በጽሑፍ ከመደረጉ በቀር ሌላ የተለየ ፍርማሊትን ስለማይጠይቅ እና የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎችም ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን ፤ የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ ወስደው ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የሸጭ ውል የፈፀሙ ሲሆን ፤ በቃላ መሃላ የተወሰደ ያላገባ ምስክር ወረቀት ካለመኖሩም በላይ ተወስዷል ቢባል እንኳን ማስረጃውን ከማሰረዝ ባለፈ የግል ንብረታቸው ላይ ተደረገው የሽያጭ ውል ፈርሶ በንብረቱ ላይ ምንም መብት የሌለው ሰው ንብረቱን እንዲከፈል የማደረግ ውጤት የሌለው መሆኑን ፤ አመልካች የንግድ መደብሩ በጋራ ተሰጥቶናል የሚል ክርክር በሥር ፍርድ አለመቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ መደብሩ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት መሆኑ ፤ የክራይ ውሉም በ1ኛ ተጠሪ ስም ብቻ በመሆኑ የንግድ መደብር ሽያጭ እና የተከራይነት መብቱ ሊተላለፍ የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ለሰበር ቅሬታው መነሻ የሆነው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ፡- አመልካች 2ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩን ሲገዙ ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረጋቸውን ፤ የንግድ መደብሩ ከአመልካች ጋር በጋራ የተሰጣቸው መሆኑ ፤ የስጦታ ውሉን ህጋዊነትና ፎርማሊትን በተመለከተ እንዲሁም የስጦታ ውሉ ለዚህ ክርክር ተብሎ በተንኮል የተዘጋጀ ነው የሚለው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ስላልተነሳ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329(1) መሠረት

ውድቅ እንዲሆን ፤ የንግድ መደብሩ ግዥ የተፈፀሙት መደብሩን 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ያገኙት የግል ንብረታቸው መሆኑን የስጦታ ውሉን በማየት የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ያላገባ ማስረጃ አይተው ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም በሰነዶችና ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በመገኘት ተገቢውን ጥንቃቄ ያደረጉ የቅን ልቦና ገዥ መሆናቸውን አረጋግጦ የንግድ መደብሩ የሚከናወንበት ቤት ባለቤት መንግስት በመሆኑ የተከራይነት መብቱ በንግድ መደብሩ ላይ የሚካሄደውን ግብይት የሚከተል በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1162(1) ፤ የንግድ ሕጉ ቁጥር 124, 151 (1) (ሀ) እና 152 ድንጋጌዎችንና በሰበር መዝገብ ቁጥር 34568 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ለሰበር ቅሬታው መሠረት የሆነው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጋራ በሰጡት መልስ ለ1ኛ ተጠሪ ያላገባ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው በቤተሰብ ቅጽ ላይ ያላገቡ በመሆኑና እሳቸውም ያላገቡ መሆኑን በቃለ መሃላ በማረጋገጣቸው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው መመሪያ አንፃር ሕገ ወጥ ተግባር ያልፈመ መሆኑንና አመልካች ቅሬታቸውን ካቀረቡ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የወሰዱትን ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲመልሱ የጠየቁ ሲሆን ፤ የቤቱ የኪራይ ውሉ በ1ኛ ተጠሪ ስም በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ያላገባ ምስክር ወረቀት ታይቶ በወቅቱ በሥራ ላይ ያለው መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት 1ኛ ተጠሪ በተከራዩት የመንግስት ንግድ ቤት ውስጥ የሚገኘውን የንግድ መደብር በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንስ ጽ/ቤት ለ2ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩን የሸጡላቸው ስለሆነ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ለ1ኛ ተጠሪ የሰጡት አገልግሎት የሌለ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተከራከሩበትን መዝገብ በትዕዛዝ በማስመጣት እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በተደረገበት የመዝገብ ቁጥር 68570 ጥቅምት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ አከራካሪው የቤት ቁጥር 249/124 የ3ኛ ወገን በመሆኑ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ የሕግ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ ተከራይ የመሆን ጥያቄም መቅረብ ያለበት ለፍርድ ቤት ሳይሆን ጉዳዩን ለሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሆኑ አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ ክፍፍልም ሆነ ኪራዩን በሚመለከት አስተዳደራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ካደረገው በኋላ አመልካች አዲስ ክስ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት አቅርበው ለሰበር ክርክሩ ምክንት የሆነው ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የንግድ መደብር የንግድ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያገለግሉ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን ፤ በሽያጭም ሆነ በሌላ በማንኛውም ውል ሊተላለፍ እንደሚችል ፤ ሽያጩን በሚመለከት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2266 እስከ 2367 ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን የቀድሞው የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ,150 እና 151 ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የንግድ መደብር ሽያጭ መሆኑ ፤ መደብሩን 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ በግላቸው በስጦታ አግኝተው በቀበሌ ንግድ ቤቱ ላይ ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ውል ገብተው ሲጠቀሙበት ቆይተው የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ተላልፎ 4ኛ ተጠሪም በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው መመሪያ ቁጥር 4/2009 መሠረት የንግድ ቤቱን የኪራይ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ስም ወደ 2ኛ ተጠሪ ስም አዙሮ 2ኛ ተጠሪ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ያመለክታል፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ አስተዳደራዊ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ ዳግም መታየት የለበትም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ታልፎ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር መገባቱ አግባብ ባይሆንም ከዚህ አንፃር ተጠሪዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 340 መሠረት የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩ በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚታይ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ በግላቸው በስጦታ ያገኙት የንግድ መደብር ባለሀብት የሆኑበትን ንብረት ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 ፤ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1204 ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 ቁጥር 24(ረ) እና የንግድ ሕጉን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር አመልካች ካቀረቡት ቅሬታ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34766 ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሁለተኛ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 33797 መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል*** ።
2. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳን ይመለስ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ሠ/ን

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 221483

ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ሰናይት አድነው

ደጀኔ አያንሳ

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ መንግስቱ ታይለማርም

2ኛ. አቶ ፈቃዱ ታይለማርም

3ኛ. አቶ ፍቅሩ ታይለማርም

4ኛ. ወ/ሮ ሰናይት ታይለማርም

5ኛ. አቶ ብርሃኑ ታይለማርም

ጠበቃ ታደሰ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሪት ሜሮን ሰይፈ ታይለማርም

2ኛ. ወ/ሪት ናርዶስ ሰይፈ ታይለማርም

3ኛ. አቶ ያፌት ሰይፈ ታይለማርም

4ኛ. አቶ አልአዛር ሰይፈ ታይለማርም

5ኛ. አቶ አበራ ፈለቀ አበራ

4ኛ ተጠሪ በራሳቸውና ስለሌሎቹም ቀረቡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

6ኛ. አቶ ሚካኤል ፈለቀ አበራ

7ኛ. ወ/ሪት ቤተልሄም ፈለቀ አበራ አልቀረቡም

8ኛ. አቶ ኤፍሬም ፈለቀ አበራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 15/06/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 200709 በቀን 29/03/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ።

ከሳሾች በቀን 02/06/2010 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከተ/ቁ 1ኛ-4ኛ የተዘረዘሩት ተከሳሾች የሟች ወንድማችን ልጆች እንደዚሁም ከተ/ቁ 5ኛ-8ኛ የተዘረዘሩት ተከሳሾች የሟች እህታችን ልጆች ናቸው፤ የሟች አባታችን አቶ ኃ/ማርያም ሀብተወልድና የሟች እናታችን ወ/ሮ የሺ ሀብተማርያም የውርስ ሀብት ተጣርቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርቦ የወራሽነት ማስረጃ ተሰጥቶናል፤ ሟቾቹ አባትና እናታችን በህይወት ዘመናቸው ያፈሩት በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቤ/ቁ 329 እና 363 የሆኑ ቤቶች ያሏቸው መሆኑ ተረጋግጦ የእነ ኃ/ማርያም ሀብተወልድ ወራሾች የሚል የነባር ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶናል፤ ይሁን እንጂ ተከሳሾች ቤቶቹን በመያዛቸው የድርሻ ክፍፍል እንድናደርግ በተደጋጋሚ ብንጠይቃቸውም ፈቃደኛ አልሆኑም። ስለዚህ ተከሳሾች ቤቶቹን ለቀው በስምምነት ወይም በጨረታ ተሸጠው በድርሻችን መጠን እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የስር ተከሳሾችም በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አስቀድመው ከሳሾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት በ27/09/2001 ዓ.ም አባታቸው ከሞቱ ከ 41 ዓመታት እናታቸው ከሞቱ ከ 27 ዓመታት በኃላ በመሆኑ እና ክስ የቀረበባቸው ንብረቶች ከ 20 ዓመታት በላይ በተከሳሾች እጅ የሚገኝ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) እና (2) እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች መሰረት ክሱ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብለዋል። በፍሬ ነገር መልሳቸው ቤቶቹ በተከሳሾች ለ20 አመትና ከዚያ በላይ የተያዙ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት እያሳደስን ቆይተናል፤ የውርስ ሀብት ያልተጣራ ሲሆን እነ በሚል በወራሾች ስም አልተዛወረም፤ የቤ.ቁ 363 ካርታው ወ/ሮ የሺ ኃ/ማርያም የሚል ነው፤ ከሳሾች ክስ ያቀረቡባቸው ቤቶች የውርስ ሀብቱ ያልተለየባቸውና በተ/ቁ 2 የተጠቀሰው ቤት ከሳሾች ባቀረቡት የወራሽነት ማረጋገጫ ውስጥ የሌለ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በድጋሚ እንዲያጣራልን በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ከሳሾች ያቀረቡት ክስ የውርስ ንብረት ክፍፍል እንጂ የውርስ ማጣራት ጥያቄ አይደለም፤ የውርስ ክፍፍል ጥያቄ ደግሞ ውርሱ ከተጣራ በኃላ በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ስለሆነ ተከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል። በፍሬ ጉዳዩ ላይም ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የውርስ ሀብት መሆናቸውና ከሳሾች የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ህ/ቁ 842(1) እና (2)፣ 1086 እና ተከታዬቹ መሰረት ተከሳሾችን ጨምሮ ድርሻቸውን ተካፍለው ሊወስዱ ይገባል፤ ተከሳሾች ቤቱን ለመጠገኛ ያወጡት ወጪ ካለ መጠኑን ገልጸው ሌላ ዳኝነት መጠየቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ተከሳሾች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ከሳሾች ወራሽነታቸውን እና ውርሱን በህጉ ግዜ ገደብ ውስጥ ሳያረጋግጡ የስር ፍ/ቤት ተከሳሾች ያነሱትን የይርጋ መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤ የስር ከሳሾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔን ሽሮታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የአመልካቾችና የተጠሪዎች የውርስ ሀብት በመ/ቁ 2056/2001 ተጣርቶ የቀረበ ስለመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት አረጋግጧል፤ በውርስ ማጣራት ሂደቱ አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪዎች የተካተቱበት ሲሆን አመልካቾች የሚች ወላጆቻችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ስለመሆናችን በውርስ ማጣራት ሂደቱ የተረጋገጠ ሲሆን በተጠሪዎች የተካደ ጉዳይ አይደለም፤ ከዚህም ባሻገር አመልካቾች ወራሽነታችንን በህጉ አግባብ ያረጋገጥን ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል። ውርስ ተጣርቶ በቀረበ ንብረት የሚጠየቅ የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ላይ የይርጋ ህግ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም። ውርስ በተጣራ ግዜ በማናቸውም ግዜ ቢሆን የውርስ ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1062 መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡበትን ግዜ ብቻ ግምት በመውሰድ በውርሱ ስለመጣራቱ ከዚህ አኳያ

የይርጋ ድንጋጌ የተፈጻሚነት ወሰን ምን እንደሆነ ሳይመለከት ውሳኔ ላይ መድረሱ ህግን ያልተከተለ በመሆኑ ሰበር ሰሚው ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ወሳኔውን እንዲያርምልን፡፡ ክርክር የተነሳባቸው ቤቶች በተጠሪዎች ስም ያልተዛወረ እና ተጠሪዎች እነዚህ የውርስ ሀብቶች ስላለመሆናቸው ወይም አመልካቾች የማይመለከታቸው ስለመሆኑ ምንም አይነት ተቃራኒ ማስረጃ አለማቅረባቸው በከፍተኛው ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ክርክር የቀረበባቸው የውርስ ሀብት የሆኑት የቤ/ቁ 329 እና 363 ቤቶች የአመልካቾችና ተጠሪዎች የጋራ የውርስ ሀብት መሆናቸውን ጭምር ከከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተጣርቶ በቀረበ የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ የይርጋ መከራከሪያ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑ በግልጽ እየታወቀ የውርስ ሀብት በአመልካቾች እና ተጠሪዎች በጋራ ተጣርቶ የቀረበ መሆኑን ወደ ጎን በማለት የአመልካቾችን ወራሽነት ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ የአመልካቾችን ጥያቄ በይርጋ ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የጠቅላይ ፍ/ቤት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ውርስ ሲጣራ የተጠሪዎች ወላጆች መኖራቸውና በወቅቱም ተቃውሞ ስለማቅረባቸው ያልተጣራ ወይም ክርክር ያልቀረበ ከመሆኑ አኳያ አሁን የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል የተባለበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ አመልካቾች በአቤቱታቸው ላይ በተደጋጋሚ ግዜ የሟች አባታችን አቶ ኃ/ማርያም ሀብተወልድ እና የሟች እናታችን ወ/ሮ የሺ ሀብተማርያም የውርስ ሀብት አመልካቾችንና ተጠሪዎችን አካቶ ተጣርቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርቦ የወራሽነት ማስረጃ ተሰጥቶናል በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ አመልካቾች ወራሽነታችን ይረጋገጥልን በሚል አቤቱታ ያቀረቡት በቀን 15/08/2001 ዓ.ም ሲሆን በ27/09/01 ዓ.ም የተጻፈ ውርስ ያጣራንበት ሪፖርት ነው በሚል ደግሞ ራሳቸው አጣርተናል በሚል በመዝገቡ ውስጥ አያይዘዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ግን አመልካቾች የሟቾች ወራሽነታቸው ተረጋግጧል በሚል ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡን ዘግቶ ተመላሽ አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን አመልካቾች በምን የህግ አግባብ እንደሆነ በማይታወቅ እና መልካም አስተዳደር በጎደለው ሁኔታ ከፍ/ቤቱ ውሳኔ ከተሰጠበት 12 ቀን በኋላ በእጅ የተጻፈ የውርስ ማጣራቱ ለማስረጃነት ይሰጥ በሚል ከውሳኔው መጨረሻ ተጽፎ ከመገኘቱ ባለፈ ተጠሪዎች በጋራ ያጣራነው እና ያቀረብነው የውርስ ማጣራት ሪፖርት

እንዲጣራልን ውሳኔ ከሰጠው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት መዝገቡ ቀርቦ እንዲታይልንና አስተያየት እንድንሰጥበት አመልክተን የስር ፍ/ቤት ግን መዝገቡን ካስመጣ በኋላ ሲመለከተው ቀድሞውኑ የውርስ አቤቱታውን በዚሁ አዲስ አበባ ፍ/ቤት ያዩት ዳኛ በመሆናቸው ቢችሉ ቀድሞ በስር ፍ/ቤት ያየሁት ጉዳይ ነው በማለት ጉዳዩ በሌላ ችሎት እንዲታይ ትእዛዝ ሊሰጡበት ሲገባ ይህን አልፈው እንዲጣራልን የጠየቅነውን አቤቱታ እና መዝገቡ ከመጣ በኋላም አስተያየት እንድንሰጥበት የጠየቅነውን አቤቱታ በምን አግባብ እንኳ እንደታለፈ ሳይገለጽልን ውሳኔ ተሰጥቷል እንጂ አመልካቾች እንደሚሉት ተጠሪዎችን በማሳተፍ የተከናወነ የውርስ ማጣራት የለም። የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ እውነታ የሚያሳየውን ማስረጃ በሚገባ ተመልክቶ በተደረገው ተገቢ ያልሆነ ተግባር እርምጃ መውሰድ እየቻለ ይህን አልፎ የቀረበለት ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሮ ውሳኔ ላይ መድረሱ ሊያስመሰግነው ሲገባ ዛሬም ይህን እውነታ ደብቀው በሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ አይመዝንም ከሚል መንፈስ ያቀረቡት አቤቱታ መሆኑን ችሎቱ ተረድቶልንና ከእኛ ተጠሪዎች ጋር በጋራ ያጣራነው የውርስ ሀብት አለመኖሩን ተረድቶልን በአመልካቾች በተደጋጋሚ ግዜ በጋራ ውርሱ ተጣርቶ ቀርቧል በሚል የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ። አመልካቾች ውርስ በህግ አግባብ አላጣሩም እንጂ ተጣርቷል ቢባል እንኳን የወራሽነት አቤቱታ ያቀረቡት የይርጋ ጊዜው ካለፈ በኃላ በመሆኑና የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ለመጠየቅ ብቻም ሳይሆን መብቱንና የውርስ ንብረቱ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከ3 አመት በኋላ የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በራሱ በህግ ባጡት መብት ላይ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነው የፌ/ከፍተኛ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፈው ብይን፤ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ክርክሩንና ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም በአመልካቾች ለስር ለፍርድ ቤት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ይዘት በአግባቡ ተለይቶ ጉዳዩን በህጉ በተዘረጋው ስርዓት በመምራት ውሳኔ የተሰጠበት ስለመሆን አለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል።

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ብይን የሰጠው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1062 ላይ ውርስ በተጣራ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ወራሾች ውርሱን ለመከፋፈል ለመጠየቅ እንደሚችሉ ተደንግጓል በሚል ነው። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ደግሞ አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ነው ያለው ከሳሾች ወራሽነታቸውን እና ውርሱን በህጉ ግዜ ገደብ ውስጥ አላረጋገጡም በሚል ነው።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሠ) እና 245 ስር እንደተደነገገው ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ እንደሚሰጥ፤ በመጨረሻም የቀረበው መቃወሚያ ከክሱ ይዘትና ከማስረጃው አንፃር ተመርምሮ መቃወሚያው ተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑን/አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ መርምሮ ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን/ትዕዛዝ ይሰጣል።

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነው ግራቀኙ በመቃወሚያው ላይ ያደረጉት ዝርዝር ክርክር የነበረ ስለመሆኑ በመዝገቡ ተመልክቶ ነገር ግን በመቅረፀ ድምፅ የተሰማው የግራ ቀኙ ክርክር በቫይረስ ምክንያት ጠፍቷል በመባሉ የመዝገቡ አካል አልተደረገም። መቃወሚያውን ለመወሰን እንዲረዳም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የመ/ቁ 2050/01 የሆነው መዝገብ እንዲቀርብ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንደነበር መዝገቡ ያሳያል። ይሁንና ይቅረብ የተባለው መዝገብ ይዘት ከተጠየቀው ዳኝነት እና ከግራቀኙ የመቃወሚያ ክርክር ጋር ስለመመርመሩ ምንም ሳይባል ከፍሏል የተጠቀሰው ብይን ተሰጥቷል።

መቃወሚያውን ከክሱ ይዘት ጋር አያይዞ በመመርመርና በአግባቡ በማጣራት፤ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች እኩል ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ እድል በመስጠት፤ እንዲሁም ለብይኑ አሰጣጥ ይረዳል ተብሎ ትዕዛዝ የተሰጠበትን መዝገብ ይዘትም ከክርክሩ አንጻር ታይቶ ብይኑ ሊሰጥ ይገባ ነበር። ይሁንና የስር ፍርድ ቤት በዝርዝር ጉዳዩን አጣርቶ በህጉ አግባብ ብይን ሊሰጥበት ሲገባ በዚህ አግባብ አይቶ አለመወሰኑን ተረድተናል። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከዚህ አንጻር ሳይመለከት መወሰኑ የሚነቀፍ ነው።

በአጠቃላይ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ይዘት በአግባቡ ሳይጤን እና ግራ ቀኙን የሚያለያያቸው የመቃወሚያ ክርክር ተገቢው ትጋት ተደርጎበት በማስረጃ በአግባቡ እንዲጣራ ሳይደረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተላለፈው ብይንና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0129743210205 በቀን 20/05/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ብይንና በቀን 29/10/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 200709 በቀን 29/03/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል።

2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች እኩል የመከራከርና ማስረጃ የማቅረብ እድል በመስጠት፤ መቃወሚያውን ለመወሰን ይረዳል በሚል እንዲቀርብ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የመ/ቁ 2050/01 የሆነ መዝገብ ይዘት በመመርመር በመቃወሚያው ላይ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 341/1/ እና 245 መሰረት መልሰናል። የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

3. ከፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ።

4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

??/? /??? 220835
?? 29/2/2015 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)
ቀነዓ ቂጣታ
ፈይሳ ወርቁ
ሰናይት አድነው
ደጀኔ አያንሳ

አመልካች - ወ/ሮ ብዙወርቅ ኃይሌ ፡- **ጠበቃ ኃ/ማርያም ተስፋዬ ቀረቡ**
ተጠሪ - 1. ወ/ሮ ገነት ጥላሁን 2. ረድኤት ከተማ 3. አቶ ትንሳኤ ከተማ
4. ወ/ሮ ቤተልሄም ከተማ ፡-**1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ ሌሎቹ አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች የካቲት 3 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 275018 ህዳር 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 101598 ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ከሟች ጋር በ1981 ዓ/ም የተጋባን ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በንብረት ላይ ምንም ድርሻ ሳይኖራት ግማሹን ትካፈል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑና ጥያቄዬ የቀረበው በወራሾች ላይ ሆኖ እና በ1ኛ ተጠሪ ላይ ዳኝነት እንደጠየኩ ተወስነዶ አቤቱታዬ በይርጋ ውድቅ መደረጉ ካለ አግባብ ነው፡፡ ሟች በ2005 ዓ/ም የሞተ በመሆኑ የይርጋ ጊዜውም ሊቆጠር የሚገባው ከ2005 ዓ/ም ጀምሮ መሆን ሲገባ ሟች የፍቺ ክስ ሲያቀርብ እኔ በሌለሁበት ሲሆን ፍ/ቤቱም ሟች ያቀረበብኝ ክስ ውድቅ ያደረገው ሆኖ እያለ ጋብቻችን እንዲፈርስ ባልወሰነበት ሁኔታ፣ ጋብቻችን ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ መፍረሱ በፍ/ቤት ተወስኗል በሚል አቤቱታዬ በይርጋ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የመቃወሚያ አመልካች (የአሁን አመልካች) ባቀረችው አቤቱታ የመቃወሚያ ተጠሪዎች (የአሁን ተጠሪዎች) ሟች አቶ ከተማ በለጠ እና የመ/አመልካች በጋብቻ ውስጥ እያለን ያፈራነውን የጋራ ንብረት በ1ኛ የመ/ተጠሪ ላይ የውርስ ንብረት ክስ አቅርበው ያስወሰኑ በመሆኑ በንብረቱ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚጎዳ ስለሆነ ይሻርልኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ የመ/ተጠሪዎችም ሟች አቶ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከተማ በለጠ በመ/አመልካች ላይ በ1994 ዓ/ም ጋብቻ እንዲፈርስለት ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱም የመ/አመልካችና ሟች በ1994 ዓ/ም የተለያዩ መሆኑን አረጋግጦ ጋብቻቸው መፍረሱን በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ2003 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የመ/አመልካች ከ1994 ዓ/ም ጋብቻቸው ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ያልጠየቀች በመሆኑ ክሷ በይርጋ ውድቅ ይሁንልን በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 101598 ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የመ/ቁጥር 19615 የሆነውን አስቀርበን እንዳየነው ሟች አቶ ከተማ በለጠ በ9/6/2003 ዓ/ም ባቀረበው ክስ ከመ/አመልካች ጋር በ1981 ዓ/ም የተጋባን ሲሆን የመ/አመልካች በ1994 ዓ/ም ግርክ አገር ሄዳ ግንኙነታቸው የተቋረጠ በመሆኑ ጋብቻችን ይፍረስልን ሲል ጠይቆ የመ/አመልካች በሌለችበት ክርክሩ ተካሂዶ ፍ/ቤቱም የመ/አመልካች እና ሟች አቶ ከተማ በለጠ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ የተለያዩ መሆኑን አረጋግጦ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በድጋሚ የፍቺ አቤቱታ የሚቀርብበት አይደለም ሲል የሟችን የፍቺ ክስ ሳይቀበለው መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሟች እና የመቃወሚያ አመልካች የጋብቻ ፍቺ በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ1994 ዓ/ም ጀምሮ መፍረሱ ተወስኗል፡፡ የፌደሬሽን ም/ቤት በሰጠው ውሳኔ ይህን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሻረው ቢሆንም ይህ ውሳኔ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ የመ/አመልካች እና የሟች ጋብቻ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት አስቀድሞ የፈረሰ በመሆኑ የመ/አመልካች ጋብቻዋ በ1994 ዓ/ም ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ሳትጠይቅ 10 ዓመት ያለፋት በመሆኑ አቤቱታዋ በይርጋ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የመ/አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 275018 ህዳር 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኝዋን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ክርክሩ በአሁን አመልካች፣ በሟች ሚስት እና በወራሾች መካከል ሲሆን ቀደም ሲል ሟች በመ/ቁጥር 19615 በሆነው ላይ ፍቺ ጠይቆ የስር ፍ/ቤት ለብዙ ጊዜ ተለያይተው ስለቆዩ ፍቺ አይወሰንም በማለት የወሰነ ሲሆን አሁን ንብረት ሊጠይቁ አይችሉም፣ የ10 ዓመት ይርጋ ያግደዋል በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መልሳቸውን አላቀረቡም፡፡ አመልካችም ሐምሌ 8 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤት መዝገብ በማስመጣት ጭምር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሟች አቶ ከተማ በለጠ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያለን በጋራ ያፈራነውን ንብረት ተጠሪዎች ተከራክረውበት ውሳኔ ያሰጡበት በመሆኑ ውሳኔው ይሻርልኝ ስትል ላቀረበችው አቤተታ የአሁን ተጠሪዎች በሟች አቶ ከተማ በለጠ እና በአመልካች መካከል ያለው ጋብቻ በፍ/ቤት በ2003 ዓ/ም በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ1994 ዓ/ም ጀምሮ መፍረሱ የተወሰነ በመሆኑና የአሁን አመልካች የጋብቻ ፍቺ ከተፈጸመበት 1994 ዓ/ም ጀምሮ በ10 ዓመት ውስጥ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ያልጠቀች በመሆኑ ክሷ በይርጋ ቀሪ ይሁንልን ሲሉ ተከራክረው የስር ፍ/ቤቶችም የአሁን አመልካችና የሟች አቶ ከተማ በለጠ ጋብቻ በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ1994 ዓ/ም ጀምሮ በ2003 ዓ/ም ፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ፈርሷል፤ አመልካች በ1994 ዓ/ም የጋብቻ ፍቺ ከተፈጸ በኋላ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በ10 ዓመት ውስጥ ስላልጠየቀች አቤቱታዋ በይርጋ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የአመልካች ቅሬታም ጋብቻችን በ2003 ዓ/ም በፍ/ቤት በተሰጠ

ውሳኔ በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ1994 ዓ/ም አልፈረሰም የሚል ነው፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ14/6/2003 ዓ/ም የተሰጠውን ትእዛዝ እንዳየነው ሚች አቶ ከተማ በለጠ ለፍ/ቤቱ በ9/6/2003 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ከወ/ሮ ብዙወርቅ ኃይሉ ጋር ያለን ጋብቻ ተጠሪ በ1994 ዓ/ም ውጪ ሀገር ሄዳ የቀረችና የማይገናኙ መሆኑን ገልጸ ጋብቻው እንዲፈርስለት ያመለከተ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ14/6/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ ቢኖርም ይህ ጋብቻ ሥልጣን ባለው አካል ቀርቦ ፍቺ ባይወሰንም ከአስር ዓመት በላይ ተለያይተው የቤተሰብ ህጉ የሚያዘው የጋብቻ ሁኔታ በመሀከላቸው ሳይኖር የቆዩ በመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤተ ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁጥር 20938 ላይ ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት በመሀከላቸው የነበረው ጋብቻ እንደቀረ የሚቆጠር በመሆኑ አመልካች አሁን በድጋሚ የፍቺ አቤቱታ ሊያቀርብ አይገባም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በመ/ቁጥር 19615 ላይ የተሰጠው የፍ/ቤት ትእዛዝ ሚች አቶ ከተማ በለጠ ከአሁን አመልካች ጋር ያለን ጋብቻ ይፍረስልኝ ሲል ህጉ በሚያዘው መሰረት ለፍ/ቤት አቤቱታ አቀርበዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤትም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 20938 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በሚች እና የአሁን አመልካች መካከል ያለው ጋብቻ ከተለያዩበት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ፈርሷል ሲል መወሰን ወይም ውሳኔ በተሰጠበት ቀን ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻቸው እንደፈረሰ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባ ነበር፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20938 ላይ በሰጠው ውሳኔ ባልና ሚስት ጋብቻቸው በፍ/ቤት ውሳኔ ሳይፈርስ፣ ጋብቻቸውን በማፍረስ ሀሳብ ከ10 ዓመት በላይ ጋብቻቸውን በማፍረስ ሀሳብ ተለያይተው፣ የየራሳቸውን ህይወት የሚመሩ እንደሆነ እና ጋብቻቸው መቼ እነደፈረሰ ለተነሳው ክርክር፣ ጋብቻቸው በተለያዩበት ጊዜ ጀምሮ እንደፈረሰ እንደሚቆጠር የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ14/6/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት በፍ/ቤቱ የተሰጠው ትእዛዝ፣ ሚች ለፍ/ቤቱ ከአሁን አመልካች ጋር ያለው ጋብቻ እንዲፈርስለት አቤቱታ ቢያቀርብለትም፣ ፍ/ቤቱ ጋብቻቸውን ሳያፈርስ አቤቱታውን ወድቅ ያደረገው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ክርክርን ከተገቢው የህጉ ትርጉም ጋር ባለማዛመድ በአሁን አመልካችና በሚች አቶ ከተማ በለጠ መካከል የነበረው ጋብቻ በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ14/6/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ፈርሷል ሲሉ የአሁን አመልካችን አቤቱታ በይርጋ ውድቅ ነው በሚል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 275018 ህዳር 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 101598 ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 19615 ላይ በ14/6/2003 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ በሚች አቶ ከተማ በለጠ እና በአሁን አመልካች መካከል ያለው ጋብቻ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ያፈረሰው መሆኑን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች አቤቱታ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ቀጣዩ ክርክር አልፎ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ከስር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ ብለናል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 220486

ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ.፡- አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ ዓ/ሕግ

2ኛ. የቢሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አስተዳደር ፅ/ቤት መኮንን ፍቃድ

3ኛ. የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር 3ኛ ክ/ከተማ ፖሊስ ፅ/ቤት ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 27/05/2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.64936 በቀን 13/05/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፆ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስም በአመልካችና በፕራይቬታይዜሽን ኤጅንሲ መካከል ጥቅምት 26 ቀን 1990 ዓም በተደረገ የግዢ እና ሽያጭ ውል መሰረት በቢሾፍቱ ከተማ ድሬ ጂቱ ቀበሌ ቁርቁራ በተባለው ቦታ የሚገኝ በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር 50/28 የተመዘገበ 113320 ካሜ ቦታ የተሰጠን ሲሆን ተጠሪዎች መስከረም 25 ቀን 2014 ዓም በጉልበት የድርጅቱን ጥበቃዎች እና የድርጅቱን ሰራተኞች በማስፈራራት ዶዘር ይዘው ወደ ግቢ በመግባት የድርጅቱን ንብረት ያወደሙ በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፤በክርክሩ መሬት ላይ አመልካች ዳኝነት ለመጠየቅ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም አመልካች በህጋዊ መንገድ የወሰደውን ይዞታ በውሉ መሰረት ለወሰደው አላማ ባለማዋሉ ጉዳት ስላስከተለ ስልጣን ባለው አካል ለህብረተሰቡ ጥቅም እንዲውል ተደርጓል፤አመልካች በመሬቱ ላይ ያፈራው ንብረት የለም፤ያወደውነውም ንብረት የለም፤አመልካች በይዞታው ላይ ያለው መብት በህጉ አግባብ የተቋረጠ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ በመቃወሚያው ላይ ያደረጉትን ክርክር መርምሮ ታህሳስ 07 ቀን 2014 ዓም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይንም አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በቀድሞው የሊዝ ስርዓት መሰረት ከመንግስት የልማት ድርጅት እና የፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ጥቅምት 26 ቀን 1990 ዓም በመግዛት ካርታ ወስዶበት በእጁ በማስገባት የዶሮ እርባታ ኢንቨስትመንት ስራ የሚያካሂድበት በመሆኑና አመልካች ዳኝነት የጠየቀው በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሰረት እንዲፈፀምለት ስላልሆነ እንዲሁም አዋጁ ሊፈፀምብኝ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ባለመኖሩ ፤ተጠሪዎች የጠቀሱት በሰበር መዝገብ ቁጥር 114622 እና 134343 የተሰጡት አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ስለሌላቸው ተጠሪዎች ከፍርድ ቤቱ ስልጣን ጋር በተያያዘ እና ከአመልካች የመክሰስ መብትና ጥቅም ጋር በተያያዘ ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ በማስከተልም ጥር 13 ቀን 2014 ዓም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔም አከራካሪው ይዞታ የአመልካች የግል ይዞታ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 4፤5 እና 6 መሰረት የከተማው መስተዳደር ለህዝብ ጥቅም ያስፈልጋል ብሎ ካመነበት ባለይዞታውን ለማስለቀቅ ስልጣን ያለው በመሆኑ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ሚያዝያ 30 ቀን 2013 ዓም ባካሄደው የካቢኔ ስብሰባ ክርክር ካስነሳው ይዞታ ውስጥ 40000 ካሜ ለልማት ስለፈለገመውሰዱን በመጥቀስ ውሳኔ ያሳለፈ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪም በ30/08/2013 ዓም በተያዘ ቃለ ጉባዔ ተመሳሳይ ውሳኔ ያሳለፈ በመሆኑ የተወሰደበት ሂደት ትክክል አይደለም፤ለህዝብ ጥቅም አይደለም የተወሰደው የሚል ክርክር አመልካች ካለው ለተገቢው የአስተዳደር አካል ክሱን ከሚያቀርብ በስተቀር ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው በማለት ክሱን ለማቅረብ

ስለማይችል፤የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለውም በተያዘ ይዞታ ላይ በመሆኑ አከራካሪው ይዞታ በልማት ምክንያት በመወሰዱ በይዞታው ላይ የአመልካች መብት የተቋረጠ በመሆኑ አመልካች ቢሮውን ለመጠየቅ ያለውን መብት ውሳኔው የማይገድበው ሆኖ የተጠሪዎች ድርጊት ሁከት አይደለም በማለት ክሱን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) መሰረት ውድቅ አድርጎታል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው የሰበር አቤቱታም ከመነሻውም የሊዝ ውል በሌለበትየሊዝ ውልህ ተቋርጧል ስለሆነም የመክሰስ መብት የለህም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም፤አመልካች በይዞታው ላይ በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተደገፈ መብት እያለው ይዞታው የተወሰደበትን አግባብ ሳያጣራ፤እየለማ የነበረን ቦታ አላለማህም በማለት ወስዶ ለመኖሪያ ሸንሸኖ በሰጠበት፤ለመኖሪያ ሸንሸኖ መስጠት ለህዝብ ጥቅም የተፈፀመ ተግባር ባልሆነበት ፤ሁከት መፈጠር አለመፈጠሩን በማስረጃ ሳያጣራ፤በሂደቱ ሳያሳትፈን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ሳይሰጠን ምትክ ቦታ ሳይሰጠንም ሆነ ካሳ ሳይከፈለን ከህጉ አግባብ ውጪ የተወሰደብን ቦታ የተወሰደብንን አግባብ ሳያጣራ ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ የተፈፀመው የሁከት ተግባር ተወግዶ በይዞታው ላይ የመጠቀም መብታችን እንዲጠበቅ ይወስንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ አመልካች ከፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የገዛው የአመልካች ይዞታ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የሊዝ ውሉ ተቋርጧል፤በዚህም ምክንያት በይዞታው ላይ መብት ስለሌለው የተፈጠረ ሁከት የለም ሲል የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1140፤1149 ድንጋጌዎችንና ስነስርዓታዊ የህግ ሂደትን/Procedural Due process of Law/ የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3) የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት የህዝብና የመንግስት እንጂ የግለሰቦች የተናጠል ሀብት ባለመሆኑ የመንግስት አካላት በግለሰቦች በተያዘ መሬት ላይ በህጉ አግባብ የሚያደርጉት ቁጥጥርና የሚወስዱትበ እርምጃ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1149 በተመለከተው የሁከት ተግባር ስር ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም፤በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 33(1) እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው የኦሮሚያ ክልል የሊዝ ደንብ ቁጥር 182/2008 መሰረት በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝን መሬት የማስተዳደር ስልጣኑ የከተማ አስተዳደሩ በመሆኑ በዚህ አግባብም የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር በከተማው የአስተዳደር ግዛት ስር በሚገኝ መሬት ላይ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር መብት ያለው በመሆኑ በህግ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ ህጉን ተከትሎ በሚወስደው እርምጃ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በክልሉ አዋጅ ቁጥር 242/2014 አንቀፅ 26(6) መሰረት የኦሮሚያ መሬት አስተዳደር ቢሮ (በተዋረድ) 2ኛ ተጠሪ በአስተዳደር ግዛቱ ውስጥ የሚገኝን በሊዝ ውልም ይሁን ከሊዝ ውል ውጪ የተሰጠን መሬት

ለታለመለት አላማ የዋለ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ በህጉ አግባብ የመውሰድ ስልጣን ያለው በመሆኑ አመልካች መሬቱን ሳያለማ ለዘመናት አጥሮ ያስቀመጠው ባዶ መሬት መሆኑን በማረጋገጥ የወሰደው እርምጃ የስራ ግዴታውን መወጣቱን እንጂ የሁከት ተግባር መፈፀሙን የሚያሳይ ባለመሆኑ፣ከአመልካች ይዞታ ውስጥ ተጠሪ ለህዝብ ጥቅም በማለት የወሰደው 40,000 ካሜ ብቻ ሲሆን ቦታው በከተማው መሪ ፕላን መሰረት ለመኖሪያ አግልግሎት የሚውል በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ሚያዝያ 30 ቀን 2013 ዓም ባደረገው ስብሰባ የቤት መስሪያ መሬት ለማግኘት በህጉ አግባብ በማህበር ተደራጅተው ለሚጠብቁት የመንግስት ሰራተኞች እንዲውል ማድረጉ በአግባቡ ስለሆነ፣በመሬቱ ላይ አንዳችም ሀብት ባላፈራበት ካሳ ይከፈለኝ ማለቱ የህግ መሰረት ስለሌለው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሳ የሚከፈለበት እና ተነሺዎች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 5(1) መሰረት በመርህ ደረጃ የሚለቀቀው መሬት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ብሎ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሰረት መሬቱ እንዲለቀቅ የመወሰን ስልጣኑ በክልል ደረጃ የክልሉ ካቢኔ ሲሆን ይህ የመወሰን ስልጣን እንደ አስፈላጊነቱ ለከተማ ወይም ወረዳ አስተዳደሩ ሊሰጥ እንደሚችል በአንቀፅ 5(5) ተመልክቷል፡፡በዚህ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት የማስለቀቅ እና የመረከብ ስልጣኑ ለከተማው ወይም ወረዳው አስተዳደር የተሰጠ መሆኑን ከአዋጁ አንቀፅ 6 ድንጋጌ የምንረዳው ቢሆንም መሬቱ ከላይ በተመለከተው አግባብ እንዲለቀቅ ግን የማስለቀቁ ሂደት በአዋጁ አንቀፅ 8 የተመለከቱትን ሂደቶች የተከተለ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡በዚህ አግባብም አስቸኳይ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ተነሺዎች ከመነሳታቸው ቢያንስ አንድ አመት አስቀድሞ ስለልማቱ አይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት እንዲያውቁና እንዲወያዩ ሊደረግ የሚገባ ሲሆን፣ስለሚነሳው ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ከመሰብሰብ ባለፈ የልኬትና መጠን መረጃ መሰብሰብ፣በተሰበሰበው ማስረጃ መሰረት የካሳ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢን ወይም ቤት በመግለፅ በፅሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት ቦታውን ከማስለቀቅ በፊት ያለ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸውን ከአንቀፅ 8 ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ገዝቶ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካወጣበት ይዞታ ውስጥ 40,000 ካሜ በተጠሪዎች እንዲወሰድ የተደረገው አመልካች በይዞታው ላይ ከወሰዱበት አላማ አንፃር ለተገቢው ልማት ባለማዋላቸው ይሁን ለተገቢው ልማት ቢያውሉትም በመሬት አጠቃቀም እቅድ

ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሰረት መሬቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ተብሎ ስለታሰበ እና ስለተወሰነ ስለመሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር አመልካች በህጋዊ መንገድ የወሰደውን ይዞታ በውሉ መሰረት ለወሰደው አላማ ባለማዋሉ ጉዳት ስላስከተለ ስልጣን ባለው አካል ለህብረተሰቡ ጥቅም እንዲውል ተደርጓል በማለት መከራከራቸውም የውል ግዴታን አለመወጣትን በአዋጁ መሰረት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታን ከሚለቀቅበት ስርዓት ጋር በማደባለቅ መከራካራቸውን ያሳያል፡፡

አመልካች በውሉ አግባብ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ይዞታውን እንዲለቁ የተደረገ ከሆነም ከመነሻውም ተጠሪዎች በውሉ አግባብ መፈፀም አለመፈፀሙን የመከታተል እና የመቆጣጠር ስልጣኑ በምን አግባብ እንዳገኙት በስር ፍርድ ቤት ሊጣራ የሚገባው ቢሆንም በዚህ አግባብ ተጣርቶ መወሰኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ ተጠሪዎች በውሉ አግባብ መፈፀም አለመፈፀሙን የመቆጣጠር ስልጣን አላቸው የሚባል ከሆነም አመልካች ይዞታው ባዶ ቦታ ከመሆን ይልቅ ለገዛበት አላማ ማለትም ለዶሮ እርባታ ስራ እያዋለው የሚገኝ ይዞታው መሆኑን ጠቅሶ የሚከራከር ከመሆኑ አንፃር የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በማስቀረብና በመስማት አከራካሪውን ፍሬ ነገር በማጥራት ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት የሰጠ መሆኑን አያሳይም፡፡

ተጠሪዎች ይዞታውን እያስለቀቁ የሚገኙት በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሰረት መሬቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ተብሎ ስለታሰበ እና በተገቢው አካል ስለተወሰነ ነው በሚል በአግባቡ የተነጠለ ክርክር የሚያቀርቡ ከሆነም አከራካሪው ይዞታ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሰረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ተብሎ ከህዝብ ጥቅም አንፃር የተሰጠ ውሳኔ አለን? በዚህ አግባብ ከመወሰኑ በፊትስ አመልካች ከመነሳቱ ቢያንስ አንድ አመት አስቀድሞ ስለልማቱ አይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት እንዲያውቁና እንዲወያዩ ተደርጓልን? ስለሚነሳው ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ከመሰብሰብ ባለፈ የልኬትና መጠን መረጃ በመሰብሰብ፣በተሰበሰበው ማስረጃ መሰረት የካሳ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢን ወይም ቤት በመግለፅ በፅሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ለአመልካች ተሰጥቷልን? በአጠቃላይ ተጠሪዎች አከራካሪውን ይዞታ እንዲለቀቅ ያደረጉት በህጉ አግባብ ተገቢውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት አመልካች ካሳና/ወይም ምትክ ቦታ የሚገባቸው ከሆነ በህጉ አግባብ ምላሽ በመስጠት ነው? ወይስ እነዚህ ሳይሟሉ በአመልካች ክስ እንደተገለፀው ተጠሪዎች በጉልበት የድርጅቱን ጥበቃዎች እና የድርጅቱን ሰራተኞች በማስፈራራት ዶዘር ይዘው ወደ ግቢ በመግባት የድርጅቱን ንብረት በማውደም? የሚሉት ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎች ተሰምተው በአግባቡ ተጣርተው ሊወሰኑ የሚገባ ቢሆንም በዚህ አግባብ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መሰጠቱን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎች ክርክር በአግባቡ ተለይቶ እና ተብራርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመስማትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሊሰጥ ሲገባ ታህሳስ 07 ቀን 2014 ዓም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን ውድቅ ያደረገውን ከመክሰስ መብትና ጥቅም አንፃር የቀረበውን መቃወሚያ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ ጥር 13 ቀን 2014 ዓም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) ን በመጥቀስ ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የክርክር አመራር ስነስርዓታዊ ግድፈት መፈፀሙን ስለሚያሳይ፣ይህ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊታረም ሲገባ መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ መሆኑን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.64936 ጥር 13 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና እና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.383907 ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁ.64936 በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ክርክር ከላይ በፍርዱ ዝርዝር በተመለከተው አግባብ በመምራትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) አግባብ መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 220476

ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ተጠሪ- ህብረት ኢንሹራንስ ኩባኒያ አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ በአሁን ታህሳስ 29 ቀን 2012 ዓ.ም ባቀረበዉ ክስ በአሁን አመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠዉ እና ንብረትነቱ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረዉ ሐበሻ ስቲል ሚልስ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሆነዉ ተሽከርካሪ በተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጠዉና ንብረትነቱ የአቶ ወርቅሸት በቀለ የሆነዉን ተሽከርካሪ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ተከትሎ ተጠሪ ብር 56,655.00 ወጪ በማድረግ አስጠግኖ መኪናዉን ለደንበኛዉ ያስረከበዉ መሆኑን ጠቅሶ መኪናዉን ለማስጠገን የወጣዉን ወጪ አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽ በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉት ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ የመጀመሪያ መቃወሚያን በማስቀደም በሰጠዉ መልስ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን መኪና ለማስጠገን የወጣዉን ወጪ የሚያስረዳ ተገቢዉን የሰነድ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤትም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል አመልካች ያቀረበዉን የመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰዉ የስር 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሽከርካሪ በፈጸመዉ ጥፋት ምክንያት መሆኑን እና ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን የደንበኛዉን መኪና ለማስጠገን ያወጣዉ ወጪ ብር 48555.00 ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ይህንኑ ገንዘብ አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽ በአንድነት በነጠላ ይክፈሉ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳት የደረሰዉ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪ ለደንበኛዉ ካሳዉን የከፈለዉ መጋቢት 26 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ እና በዚህም ምክንያት ክሱ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2143 መሠረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 2143 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 178220 እና 194880 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ያላገናዘበ መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል።

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም ክሱ በይርጋ አይታገድም በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል። በዚህም መሠረት ተጠሪ ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳት የደረሰዉ አመልካች በአቤቱታዉ የጠቀሳቸዉ የሰበር ዉሳኔዎች ከመወሰናቸዉ በፊት በ2007 ዓ.ም በመሆኑ ዉሳኔዉ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጸንቶ እንዲወሰንለት ጠይቋል። አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳት የተከሰተዉ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ስለመድረሱ እና ተጠሪም በጉዳቱ ምክንያት ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉን ካሳ ለደንበኛዉ የፈጸመዉ መጋቢት 26 ቀን 2007 ዓ.ም ስለመሆኑ ተጠሪ ክዶ አይከራከርም። ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ ጉዳቱ የደረሰበትን መኪና ባለቤት በመተካት ሲሆን፣ አመልካችን ለክሱ ተጠሪ አድርጎ የሰየመዉም ለጉዳት አድራሹ መኪና የመድን ሽፋን ሰጥቷል በሚል ምክንያት በመሆኑ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለዉ ግንኙነት የሚገዛዉ ከዉል ዉጪ ኃላፊነትን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ ላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ነዉ። በዚህ ሰበር ችሎት ግራ የሚከራከሩበት ጭብጥ ይርጋን የሚመለከት በመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በህጉ አንቀጽ 2143 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል። የህጉ አንቀጽ 2143(1) ከዉል ዉጪ ጉዳት

የደረሰበት ሰዉ የጉዳት ካሳ ለመጠየቅ ክስ ማቅረብ የሚችለዉ ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ስለመሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 178220 እና 194880 (ያልታተሙ) እና በሌሎችም በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ በአደጋዉ ምክንያት ጉዳት የደረሰበትን ተጎጂ በመተካት ክሱን ማቅረብ ያለበት ለተጎጂዉ ካሳዉን ከከፈለ በኋላ ወይም ጉዳቱ የደረሰበትን መኪና ካስጠገነበት መጋቢት 26 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በሚቆጠር ሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ ነዉ፡፡ ይሁንና ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ መኪናዉን ለተጎጂዉ ካስጠገነበት ጊዜ አንስቶ ሲቆጠር አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉን የይርጋ መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ላይ አከራክሮ የሰጠዉ ዉሳኔ የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 2143 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን ጨምሮ በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የሰጣቸዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 282356 ላይ የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 270665 ላይ ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ ተብሏል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 220416

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አቡ ታዬ፡- ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወጣት ሚኪያስ በድሉ ፡- ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሊሻን አምሜ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዉርስ ድርሻ አስለቅቆ ለመረከብ በቀረበ ክስ መነሻ በሌላ መዝገብ ላይ እንደዉሉ እንዲፈጸም ፍርድ ያረፈበት የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በ2ኛ ተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ዉስጥ የቤት ቁጥር 36AB የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ያለ መኖሪያ ቤት ንብረትነቱ የአባቱ የዉርስ ሀብት ነዉ፡፡አባቱ በቀን 05/07/1996ዓ/ም በመሞቱ 2ኛ ተጠሪ እናቱ የሟች ሚስት መሆኗንና 1ኛ ተጠሪ እና እህቱ ሕጻናት ስለነበርን አሳዳጊ መሆኗን በመ/ቁጥር 1644/96 ላይ አስወስናልች፡፡ ይህ የአባታችን ሀብት በዉርስ ተላልፎልናል፡፡በወርስ የተላለፈልንን 4 ክፍል ያለዉን ይህንን ቤት 2ኛ ተጠሪ በወር1500.00 ገቢ እየሰበሰበች እየተጠቀመች ትገኛለች፡፡1ኛ ተጠሪ በአሁኑ ጊዜ እድሜዬ 19

ዓመት ስለሆነ በዉርስ በተላለፈልኝ መኖሪያ ቤት ላይ የእህቱ ድርሻ 50 በመቶ ሲሆን የእኔ የ1ኛ ተጠሪ የዉርስ ድርሻ ደግሞ 50 በመቶ ነዉ፡፡ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ የእኔን ድርሻ እንድትለቅልኝ እንዲሁም የ14 ዓመት የቤት ኪራይ ገቢ በመሰብሰብ ለራሷ ጥቅም ያዋለች በመሆኑ ከኪራይ ገቢ 50 በመቶ ድርሻዬን እንዲትሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ንብረት በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14679 እና 15574 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ለአቶ አቡ ታዬ በሽያጭ የተላለፈ ነዉ፡፡ቤቱ ተሸጦ ከተገኘዉ ገንዘብ በብር 355,000.00 በጋራ ለጎ ቀበሌ ዉስጥ መኖሪያ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ ቤት ገዛሁለት እንጂ ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም፡፡የቤት ኪራይን አስመልክቶ አባቱ ከሞተ በኋላ ከብር 600.00 ባልበለጠ 4 ክፍል በማከራየት የሚገኘዉን ገንዘብ ለምግብ፣ለልብስ እና ለትምህርት ለተለያዩ ክፍያዎች ለእነሱ ጥቅም አዉያለሁ፡፡ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ይህንን እያወቀ ያቀረበዉ ክስ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸዉ በአመለከቱት መሰረት በአቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 15574 በሆነዉ ላይ 2ኛ ተጠሪ ሽጠዉ ለሕጻናቱ ጥቅም እንዲያዉሉ በተወሰነዉ መሰረት አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ላይ በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ ዉል የገዛሁት ነዉ፡፡ቤቱ በዚህ መልኩ መሸጡንና ዉሉም እንዳልፈረሰ 1ኛ ተጠሪ እያወቀ ያቀረበዉ ክስ የእኔን መብት የሚጎዳ ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመ ሀብት በአመልካች ስም እንዲያዛዉሩ ክስ ቀርቦባቸዉ በመ/ቁጥር 15832 ላይ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ስለሆነም አስቀድሞ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ የቀረበ ክስ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 15969 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 25/06/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት አመልካች በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ዉል በብር 450,000.00 በመግዛት ገንዘቡን በባንክ መክፈሉ ተረጋግጧል፡፡የቤት ሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ ስንት ነዉ የሚለዉን ለማጣራት የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ 1ኛ ተጠሪ በቀን 01/11/1993ዓ/ም እንደተወለደ መረዳቱን በመግለጽ ዉሉ ሲደረግ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ 17 ዓመት ከ4 ወር ከ7 ቀን ነበር የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ከመሸጣቸዉ በፊት የ1ኛ ተጠሪን ወራሽነት በመ/ቁጥር 14697 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ አረጋግጠዋል፡፡በመቀጠል ይህንን ቤት በመሸጥ ለሕጻናቱ ጥቅም ማዋል እንዲችሉ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15574 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ፈቃድ አግኝተዋል፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ ዉል በሽያጭ ለአመልካች ያስተላለፉት በዚህ መልኩ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከአገኙ በኋላ በመሆኑና አመልካችም ይህንን የፍርድ ቤት ፈቃድ በማየት ዉሉን በቅን ልቦና ስለተዋዋሉ የሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸዉ ናቸዉ፡፡1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ከሥልጣናቸዉ በላይ በማለፍ የፈጸሙት ተግባር ካለ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ መጠየቅ ከሚችል በስተቀር 3ኛ ወገን የሆነዉ አመልካች የሕግ አካሄድ ጠብቆ ንብረቱን በመግዛት ያገኘዉን የንብረት መብት በማሳጣት ሊሆን አይገባም፡፡እንዲሁም 2ኛ

ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ከአስተላለፉ በኋላ ገንዘቡን ለወራሾች ጥቅም ለማዋል በብር 355,000.00 ሌላ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ መግዛታቸዉን 1ኛ ተጠሪ አልካደም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46490 በሰጠዉ ዉሳኔ ለልጆች ጥቅም ንብረቱ የተሸጠ ከሆነ ዉሉ በማንኛዉም አይነት የማይፈርስ መሆኑን የሕግ ትርጉም ስለሰጠ የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡እንዲሁም ቤቱ ከፈቃዴ ዉጭ ተሸጧል የሚል ከሆነም በሰ/መ/ቁጥር 41857 እና 47378 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን መጠየቅ ከሚችል በስተቀር ቤቱን በሽያጭ ያገኙትን አመልካችን መጠየቅ አይችልም፡፡ስለሆነም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በሽያጭ የተላለፈ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከዚህ ቤት ላይ የዉርስ ድርሻ ይሰጠኝ በማለት ያቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ በማድረግ ቤቱ ተከራይቶ ከተገኘዉ ከብር 166,600.00 ገቢ ላይ 2ኛ ተጠሪ 50 በመቶዉን ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

1ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 36714 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 06/11/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ዉሉ በተፈጸመበት ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ 20 ዓመት ሞልቶት ከሞግዚት ነጻ ሆኖ ዉል ለመዋዋል በሕግ ችሎታ የገኘበት ጊዜ ሆኖ እያለ ዉሉን 2ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ የሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ ቀሪ ከሆነ በኋላ ከአመልካች ጋር መዋዋላቸዉ ዉሉን ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት ነዉ፡፡በመሆነም የቤት ሽያጭ ዉል ፈርሶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1815/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 382451 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 04/05/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤት ሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ ለአቅመ አዳም ደርሷል በሚል የደረሰበትን ድምዳሜ በመቀበል ክርክር ካስነሳዉ ቤት ላይ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ 50 በመቶ ብቻ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ የሆነዉን የቤቱን 50 በመቶ ብቻ ሊለቁ ይገባል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤቱን የገዙበትን ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ማስመለስ ይችላሉ በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡ቀጥሎም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 392365 ላይ በቀን 25/05/2014ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የሰበር አቤቱታቸዉን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 26/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-1ኛ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ የዉርስ ንብረት ድርሻ ይሰጠኝ በሚል ዳኝነት የጠየቀበት ነዉ፡፡በቀን 08/04/2011ዓ/ም የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ ዳኝነት አልጠየቀም፡፡የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት ባልተጠየቀበት የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በዉሉ መሰረት እንዲፈጸም በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

15832 ላይ ክርክር ተደርጎ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምና የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘገብ በቀን 22/05/2011ዓ/ም ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህ ዉል እንዲፍርስ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጸመበት ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን የሸጡት በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15574 ላይ በቀን 05/04/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሸጠዉ ለልጆች ጥቅም እንዲያዉሉ በተፈቀደላቸዉ መሰረት ነዉ፡፡አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል የገዛሁት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ በፍርድ ቤት ፈቃድ የተሰጣቸዉ መሆኑን፣2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪና የእህቱ ሞግዚት እና 1ኛ ተጠሪና እህቱ ደግሞ የሚች አባታቸዉ ወራሽ መሆናቸዉን የሚያሳዩ ዉሳኔዎችን በማረጋገጥ ነዉ፡፡እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሸጠዉ በተቀበሉት ገንዘብ በ1ኛ ተጠሪና በእህቱ ስም በቀን 11/04/2011ዓ/ም በብር 355,000.00 ሌላ ቤት እንደገዙላቸዉ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በዚህ አግባብ አመልካች ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ በቅን ልቦና የገዛሁት ቤት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሰኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 47378፣ 41857 እና 46490 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ በተጨማሪም 1ኛ ተጠሪ መብቱ ተነክቶበት ከሆነ ከ2ኛ ተጠሪ ይጠይቃል እንጂ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ሊወሰን ስለማይገባ ከዚህም አኳያ ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በአቀረበዉ ክስ እድሜዉ ተጣርቶ እንዲወሰን ዳኝነት ባልጠየቀበት እንዲጣራ መደረጉ ስህተት ነዉ፡፡እድሜዉን ማጣራት አስፈላጊ ነዉ ቢባል እንኳን የዉርሱ በተጣራበት በመ/ቁጥር 14697 እና በመ/ቁጥር 15574 ላይ በቀን 21/03/2011ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ 17 ዓመት እንደሆነ የተገለጸበት ዉሳኔ በማስረጃነት ቀርቦ እያለ ይህ ማስረጃ ሳይታይ ዉሳኔዎቹም እንደ ምስክር ወረቀት የሚታዩ ዉሳኔዎች(Declaratory Judgment) እንደመሆናቸዉ በመ/ቁጥር 1644/96 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከሌሎች ተመሳሳይ ዉሳኔዎች ላይ ከተገለጸዉ የበለጠ ዋጋ የሚያገኝበት ምክንያት ሳይኖር በማስበለጥ የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

በተጨማሪም በቀን 08/04/2011 ዓ/ም የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል በተመለከተ በመ/ቁጥር 15832 ላይ ክርክር ተደርጎ በቀን 22/05/2011ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸም ተወሰኖ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ሆኖ እያለ አመልካች ይህንን መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ ስገባ የስር ፍርድ ቤቶች ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሰረት በፍርድ ያለቀ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ አለመወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለመሸጥ ሥልጣን የተሰጣቸዉ ስለመሆኑና አመልካችም የተሰጠዉን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ ገዝተዉ የስም ዝዉዉር

እንዲፈጸም ተወስኖ እያለ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲለቀቅ የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች መልሳቸዉን አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 22/06/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን የአቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- የሞግዚትነት ሥልጣን ለሞግዚት የሚሰጠዉ የሞግዚት ተደራጊዉ እድሜ ሲታወቅ ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆኑ እንዲወሰን በመ/ቁጥር 1644/96 ላይ ስትጠይቅ የ1ኛ ተጠሪ አድሜ 5 ዓመት እንደሆነ በራሷ እጅ ጽሁፍ ለፍርድ ቤቱ አሳዉቃለች፤በምስክሮችም አስረድታለች፡፡ይህንንም ተከትሎ ፍርድ ቤቱ 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪ ሞግዚት እንድትሆን ወስኗል፡፡ከዚህ በኋላ ለ2ኛ ተጠሪ ሌላ የሞግዚትነት ሥልጣን አልተሰጣትም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14697 እና 15574 የተሰጡ ዉሳኔዎችን በማለፍ በመ/ቁጥር 1644/96 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉን የ1ኛ ተጠሪን እድሜ መሰረት አድርጎ የቤት ሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ 1ኛ ተጠሪ ለአቅሜ አዳም የደረሰ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ፡፡ በመ/ቁጥር 1644/96 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት የቤት ሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ ለአቅሜ አዳም እንደደረሰ ተረጋግጧል፡፡በዚህ ምክንያት አመልካች የቤት ሽያጭ ዉሉን 2ኛ ተጠሪ መዋዋል እንደማትችል እያወቁ በመከነ የሞግዚትነት ሥልጣን መዋዋሉ ተረጋግጦ ዉሉ እንዲፈርስ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንድትሸጥ እንዲፈቀድላት በመ/ቁጥር 15574 ላይ ያመለከተችዉ በቀን 04/04/2011ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ ሆኖ አቤቱታዋ ተመርምሮ ዉሳኔ የተሰጠዉ ደግሞ በቀን 05/04/2011 ዓ/ም መሆኑን በማየት የ2ኛ ተጠሪ ለምን እደፈጠኑ እያወቁና ማወቅ ሲገባቸዉ ለወደፊት ከሚመጣባቸዉ ኃላፊነት ለመሸሽ ዉሳኔ ማሰጠታቸዉን ስለሚያሳይ አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረቡት ክርክር ዉድቅ መደረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ዉሉ በተደረገ ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ 20 አመት ስለሆነ በመ/ቁጥር 15832 ላይ 2ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ሥልጣን ከአመልካች ጋር ስለዉል አፈጻጸም ተከራክራ የተሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪን የማያስገድድና እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ነዉ፡፡አመልካች ቤቱን ለመግዛት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ በፍርድ ቤት ፈቃድ እንደተሰጣት ብቻ ሳይሆን የጸና ዉክልና እና የሞግዚትነት ሥልጣን እንዳላት ጭምር ማረጋገጥ ሲገባቸዉ ያላረጋገጡ በመሆኑ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዋል ሊባል አይችልም፡፡ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ ባሰሙት ክርክር መነሻ የሞግዚትነት ስልጣን ከአበቃ በኋላ የተደረገ ዉል መሆኑ ተረጋግጦ ዉሉ እንዲፈርስ በዚሁ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰ/መ/ቁጥር 153664 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ዉሉም ስልጣን ባለዉ አካል ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪን ስለማያስገድድ ክስ በመመስረት ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይገባኝም፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የጸና የሞግዚትነት ሥልጣን የላትም እንጂ መሀል ከተማ ላይ የሚገኝ ሕጋዊ መኖሪያ ቤት ሽጣ ከከተማ ዉጭ የሆነ ሕገ-ወጥ የጨረቃ ቤት መግዛቷ ቤቱን የሸጠችበትን ገንዘብ ለልጆች ጥቅም አዉላለች የሚያስብል ባለመሆኑ ከዚህም አንጻር የቀረበዉ ክርክር ሚዛናዊነት የገደለዉና በሰ/መ/ቁጥር 46490 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡በመሆኑም ዉሉ እንዲፈርስና 1ኛ ተጠሪ የዉርስ ድርሻዬን እንዳገኝ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 22/06/2014ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ 1ኛ ተጠሪ ክስ የመሰረተዉ የዉርስ ንብረት ድርሻ ይሰጠኝ በሚል እንጂ በቀን 08/04/2011ዓ/ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ አይደለም፡፡ አመልካች ክስ መስርቶብን የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈጸም በመ/ቁጥር 15832 ላይ በቀን 22/05/2011ዓ/ም ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ቤቱን የሸጥኩት ቤቱ ተሸጦ በሚገኘዉ ገንዘብ ለልጆች ጥቅም እንዳዉል ፍርድ ቤት በፈቀደልኝ መሰረት ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ እና በእህቱ ሜሮን በድሉ ስም ቤት በመግዛት ገንዘቡን ለጥቅማቸዉ አዉያለሁ፡፡የሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ 17 ዓመት ከ4 ወር ከ7 ቀን መሆኑ በማስረጃ ከመረጋገጡም በተጨማሪ ልጁ 1ኛ ተጠሪ የተወለደበትን ቀን የማዉቀዉ እኔ እናቱ ሆኜ እያለሁ በተቃራኒዉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የሰጡት ዉሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ቢወሰን ተቃዉሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት 2ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ሥልጣን ከአመልካች ጋር የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ዉል ፈርሶ የቤቱ 50 በመቶ ለ1ኛ ተጠሪ ሊለቀቅለት ይገባል ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ በቀን 22/04/2011 ዓ/ም ሲሆን የክሱ ስረ ነገር የዉርስ ሀብት ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የክሱ ምክንያት ደግሞ እድሜዉ 19 ዓመት መሆኑንና እናቱ 2ኛ ተጠሪ የአሳዳጊነት ኃላፊነታቸዉን እየተወጡ ባለመሆኑ የዉርስ ሀብት ነዉ ተብሎ በክሱ ከተጠቀሰዉ ቤት 50 በመቶ የዉርስ ድርሻ ለቀዉ እንዲያስረክቡት እና የቤቱ ኪራይ ገቢ ላይ ድርሻዉ እንዲከፈለዉ ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱ በፍርድ ቤት ፈቃድ ተሸጦ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ወደ ገዥ ስም የዞረ ከመሆኑም በተጨማሪ ከሽያጩ የተገኘዉ ገንዘብም ሆነ ከኪራይ የተገኘዉ ገቢ ለ1ኛ ተጠሪና ለእህቱ ጥቅም የዋለ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም ቤቱን ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ ገዝተዉ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸም በፍርድ በተወሰነዉ መሰረት በስማቸዉ ዞሮ የተመዘገበ በመሆኑ በቤቱ ላይ የቀረበዉ ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ ገብተዉ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት የቀረበዉን የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ አመልካች ቤቱን በሕግ አግባብ ገዝተዉ የያዙት እንደሆነ በማስረጃ እንዳስረዱ በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስለቀቅ ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ 1ኛ ተጠሪ ለአቅመ አዳም ደርሶ ከሞግዚት ሥልጣን ሥር ያልነበረበት ጊዜ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በሚል የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ በሆነዉ የቤቱ 50 በመቶ ላይ የተደረገዉ ዉል ፈርሶ 2ኛ ተጠሪ የቤቱን 50 በመቶ ለ1ኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስነዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት የ1ኛ ተጠሪ እና የእህቱ ሜሮን በድሉ የወርስ ሀብት የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ።2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ እና የሜሮን በድሉ ሞግዚት የነበሩ መሆኑ እንዲሁም እናታቸዉ እንደሆኑ አከራካሪ አይደለም።ይህ የወርስ ሀብት የነበረዉ ቤት አመልካች ይዞታ ስር የሆነዉ 2ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ሥልጣን ከአመልካች ጋር በቀን 08/04/2011ዓ/ም በአደረጉት የሽያጭ ዉል መነሻ አመልካች በመግዛታቸዉ ምክንያት መሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊሸጡ የቻሉት በሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ ከመሆኑም በተጨማሪ በወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15574 ላይ በቀን 05/04/2011ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ቤቱን ሸጠዉ ሞግዚት ለሆኑላቸዉ ለ1ኛ ተጠሪ እና ለእህቱ ሜሮን በድሉ ጥቅም እንዲያዉሉ በተሰጣቸዉ ፈቃድ መሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች በዉሳኔያቸዉ አረጋግጠዋል። አመልካች በሽያጭ ዉሉ መሰረት አልተፈጸመልኝም በማለት በመሰሩቱት ክስ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15832 ላይ በቀን 22/05/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈጸምና የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘገብ ተወስኖ በአሁኑ ጊዜ በአመልካች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝም ከክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እና ግራ ቀኙ ለዚህ ችሎት ካሰሙት ክርክር ተገንዝበናል።

ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ የ1ኛ ተጠሪ እድሜ ለአቅመ አዳም ደርሶ እያለ 2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ ጸንቶ እንደሚገኝ አድርገዉ ከፍርድ ቤት ፈቃድ በመቀበል ከአመልካች ጋር የቤት ሽያጭ ዉል መዋዋላቸዉ ምክንያት ሆኖ እንደዉሉ እንዲፈጸም በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቶ እያለ 1ኛ ተጠሪ የወርስ ድርሻ ክፍያ በመጠየቅ ባቀረቡት ክስ መነሻ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ሕግን የተከተለ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ።

አመልካች ቤቱን በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገ ዉል ሊገዙ የቻሉት 2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣናቸዉን ተጠቅመዉ ቤቱን ሸጠዉ ለ1ኛ ተጠሪና ለእህቱ ጥቅም እንዲያዉሉ በመፍቀድ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15574 ላይ በቀን 05/04/2011ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመመልከት ነዉ። ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሸጥ አስቀድሞ የሚመለከተዉን ፍርድ ቤት ማስፈቀድ እንዳለበት በኦሮሚያ ክልል በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ ላይ በግልጽ ባይደነገግም የማይንቀሳቀስ ንብረት በአገራችን ካለዉ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ሞግዚት ፍርድ ቤትን ማስፈቀድ ሳያስፈልገዉ በፈለገዉ ጊዜ የሞግዚት አድራጊዉን ሕጻን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ይችላል የሚል አቋም በሕግ አዉጪዉ ተይሂል ብሎ ለመደምደም የሚቻል ባለመሆኑ ሞግዚት ለሕጻኑ አስተዳደግ የሕጻኑን የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ የግድ እንደሚል ካመነ በሽያጭ ከማስተላለፉ በፊት የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 194876 ላይ በቀን 28/08/2013ዓ/ም(ያልታተመ) አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።ከዚህ አኳያ ሲታይ አመልካች የቤቱን ሽያጭ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የተዋዋሉት ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጣቸዉን ቤት ለመሸጥ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ በማየት በመሆኑ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ የፈጸሙት ዉል መሆኑን አመላካች ነዉ።

ማስታወሻ፣ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ማለት የከሳሽን መብት ለመመስረት የሚያስችል እና/ወይም ለተከሳሹ መከላከያ ለመሆን የሚችል በክስ አቤቱታ፣ በመከላከያ መልስ፣ በማስረጃ ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ተከራካሪዎች ተመርምረዉ በሰጡት መልስ ላይ እና በሕግ ላይ ተመስርቶ ግራ ቀኙ የተካካዱበትን የክርክር ነጥብ መሰረት ተደርጎ ለተጠየቀዉ ዳኝነት ዉሳኔ ለመስጠት የሚያዝ ነዉ፡፡አመልካች አከራካሪዉን ቤት ጥንቃቄ ሳያደርጉ ገዝተዋል ቢባል እንኳን ይህ ጉዳይ አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ ሊቀርብ እና ሊመረመር የሚችለዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ተጠይቆበት የቀረበ ክስ ሲኖር ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ የዉርስ ድርሻዉን አስለቅቆ ለመረከብ እንጂ 2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ ከአበቃ በኋላ የዉርስ ድርሻዉን ለአመልካች በሽያጭ ማስተላለፋቸዉን እንዲሁም የሸያጩን ገንዘብ ለእርሱ ጥቅም አለማዋላቸዉን ምክንያት በማድረግ በቀን 08/04/2011ዓ/ም የተደረገ ዉል እንዲፈርስ ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረበዉ ክስ የለም፡፡በዚህ መልኩ በቀን 08/04/2011ዓ/ም የተደረገዉን የቤት ሽያጭ ዉል ለማስፈረስ ዳኝነት ተጠይቆ ክስ ባልቀረበበት ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያዩት ክልሉ ፍርድ ቤቶች ይህ የቤት ሽያጭ በተፈጸመበት ጊዜ 1ኛ ተጠሪ እድሜ ለአቅመ አዳም ደርሶ የ2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣን ማብቃት አለማብቃቱን በተመለከተ ጭብጥ መስርተዉ በማስረጃ እንዲጣራ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ በጊዜዉ ለአቅመ አዳም ደርሶ ነበር የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን የጭብጥ አመሰራረት ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ እንዲሁም በዚህ መልኩ የተሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት ተጠይቆበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ዉሳኔ ሳይሰጥ ያለፈበት የክርክር ነጥብ ካልሆነ በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኝነት ተጠይቆ ክርክር ባልተደረገበት ነጥብ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንደማይችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/2 እና 329/1 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ፡፡

በተጨማሪም በቀን 08/04/2011ዓ/ም በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል መሰረት እንዲፈጸም ዳኝነት በመጠየቅ አመልካች በዚያዉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15832 ላይ ክስ መስርተዉ 2ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ሥልጣን ተካክረዉ ፍርድ ቤቱ በቀን 22/05/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምና የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘገብ ዉሳኔ እንደሰጠ ተረጋግጧል፡፡በዚህ መልኩ የተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እስከአሁን ጸንቶ የሚገኝ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ከፍርድ ውጭ ያሉ የንብረት ሀብትነት ማስተላለፍ ተግባሮች ለተላለፈለት ሰው ቀድሞ ያልነበረውን አዲስ መብት የሚፈጥሩ ሲሆኑ ፍርድ ግን አዲስ መብት የሚገኝበት ሳይሆን የነበረ ግን ያልተከበረ መብት የሚከበርበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚሰጥ ፍርድ ፍርዱ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር ግንኙነት በአለዉ ማንኛውም ሰው ላይ ፍርዱን አንዲያከበር ግዴታ የሚጥል ሲሆን ይህም የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት አንዱ ገጽታ ነው፡፡ ፍርድ የሚለወጠው ወይም የሚሻሻለው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ እና አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ በግልጽ በተመለከቱት ሥርዓቶች ብቻ በመሆኑ በፍርድ መብቱ የተነካበት ወገን በየደረጃዉ በይግባኝ እና በሰበር አቤቱታ በማቅርብ አለያም

ሥነ ሥርዓት ሕጉ በዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ፍርዱን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት ፍርዱን በመቃወም ማመልከቻ በማቅረብ የተጓደለበትን መብት ማስከበር ይችላል፡፡

በተሰጠዉ ፍርድ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነክቶብኛል የሚል ሰዉ ፍርዱን በመቃወም ማመልከቻ የሚያቀርብበትና ክርክሩ ተሰምቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሥነ ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት በተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ መብቴ ተነክቷል በማለት አቤቱታ ያቀረበዉ ሰዉ ክርክር ባስነሳው ጉዳይ ላይ የሚያገባው እና ቀድሞም ተከራካሪ መሆን የሚገባው ከነበረና ፍርዱን በመቃወም ማመልከቻ ከአቀረበ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 360(1 እና 2) እንደተመለከተው በማመልከቻው ላይ አስቀድሞ በክርክሩ ዉስጥ የነበሩ ተከራካሪዎች መልስ የሚሠጡበት እና ጉዳዩ ላይ እንደገና ሙሉ ክርክር የሚደረግበት ሥነ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ውጤቱም ቀድሞ የተሠጠውን ፍርድ መለወጥ ወይም ማሻሻል ድረስ ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የነበረዉ መብት አንድም በቀን 08/04/2011ዓ/ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈጸምና የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘገብ አመልካች ዳኝነት ጠይቀዉ 2ኛ ተጠሪም በሞግዚትነት ሥልጣናቸዉ ተከራክረዉ በዉሉ መሰረት እንዲፈፀምና የቤቱ ስመ ሀበት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘግብ ዉሳኔ በተሰጠበት በመ/ቁጥር 15832 ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 2ኛ ተጠሪ ሲሸጡ እድሜዉ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ እና የ2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣን ያበቃ መሆኑን በመግለጽ እንደዉሉ ሊፈጸም አይገባም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ጣልቃ በመግባት መብቱን ማስከበር ነበር፡፡ አለያም ክርክሩ መኖሩን ሳያዉቅ ፍርድ ተሰጥቶ ከሆነም መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት እንደዉሉ ሊፈጸምና የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ሊዞር አይገባም በማለት በመቃወም ተከራክሮ መብቱን በማስከበር ነዉ፡፡

በአንድ የፍርድ ዉሳኔ ላይ ያለዉ ማንኛዉም ስህተት ሊታረም የሚችለዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓትና በሌሎች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት አግባብ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት በመመራት የፍርድ ዉሳኔዉ እንዲታረም ካልተደረገ የፍርድ ዉሳኔዉ የሚኖረዉን ዉጤት በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 ላይ ተደንግጓል፡፡ዉጤቱም የሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ ያልታረመ ዉሳኔ ከእነጉድለቱም ቢሆን በጉዳዩ ላይ ተቀባይነት ያለዉና የመጨረሻ ይሆናል የሚል ነዉ፡፡1ኛ ተጠሪ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ ፍርዱን በመቃወም አመልክቶ መብቱን ያስከበረ ወይም የፍርድ ዉሳኔዉን ያስለወጠ ስለመሆኑ በመግለጽ ያሰማዉ ክርክር የለም፡፡በዚህ አግባብ ክርክር ቀርቦ ፍርዱ እስካልተለወጠ ድረስ በቤት ሽያጭ ዉሉ መሰረት ተፈጽሞ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ እንዲመዘገብ በወረዳ ፍርድ በመ/ቁጥር 15832 ላይ በቀን 22/05/2011ዓ/ም የተሰጠዉን ዉሳኔ ዋጋ አልባ የሚያደርግ ዉሳኔ በሌላ መዝገብ ላይ በቀረበ ክስ መነሻ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ብሎ መወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ይሆናል፡፡እንዲሁም በዚህ መልኩ ክርክር መምራት ክርክሮች በሥነ ሥርዓት ሕግ ከተደነገገዉ አግባብ ዉጭ በዘፈቀደ እንዲመሩና ምክንያታዊ በሆነ

አጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እንዲቋጩ ሥነ ሥርዓት ሕጉ የያዘዉ ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ ያደርጋል፡፡በዚህ መልኩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ከግብ እንዳያደርስ በሚያደርግ መልኩ ክርክሩን በመምራት አስቀድሞ የተሰጠዉን ፍርድ ዋጋ አልባ በሚያደርግ መልኩ ፍርድ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 67127 ላይ (በቀጽ 13 እንደታተመዉ) አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ሲጠቃለል 1ኛ ተጠሪ 50 በመቶ የዉርስ ድርሻዬ ነዉ ያለዉን መኖሪያ ቤት አመልካች በግዥ ማግኘታቸዉና የቤቱ ባለቤትነት በስማቸዉ ዞሮ ተመዝግቦ ቤቱ በይዞታቸዉ ስር ሊሆን የቻለዉ በቤት ሽያጭ ዉሉ መሰረት እንዲፈጸም በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ መሰረት መሆኑ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡እኛም ይህንኑ ተገንዝበናል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መብቱ ተነክቷል የሚል ከሆነ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደዉ አግባብ ዉሳኔዉን ማስለወጥ ከሚችል በስተቀር የዉርስ ድርሻዉ እንዲሰጠዉ ዳኝነት በመጠየቅ ባቀረበዉ ክስ መነሻ እድሜዉ ለአቅመ አዳም መድረስ አለመድረሱ እንዲጣራ መደረጉም ሆነ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስና በቤት ሽያጭ ዉሉ መሰረት እንዲፈጸም የተሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ እንዲያጣ ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር ባዩት በክልሉ ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢዉን የክርክር አመራር የተከተለ አይደለም፡፡በመሆኑም በዚህ አግባብ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 67127 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡በሌላ በኩል የወረዳዉ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር በመቀበል የ1ኛ ተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ ከላይ በዝርዝር በተመለከትነዉ መሰረት ምክንያቱን በመለወጥ ከዉጤት አንጻር ተገቢ ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36714 ላይ በቀን 06/11/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 382451 ላይ በቀን 04/05/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 392365 ላይ በቀን 25/05/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15969 ላይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስለቀቅ ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ በቀን 25/06/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡ ሌላዉ የወሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. የፍርድ አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የፍርድ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ ትእዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 220119

ጥቅምት 1 ቀን 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ አብዱልረሺድ ኤልሚ መሳ ፡- አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ሀብታሙ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡1ኛ/ ወ/ሮ ዘይነባ ነጊዬ ሆሽ ቀረቡ

2ኛ/ አቶ ኤሊያስ አህመድ እስማኤል፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ዉሳኔዉ እንዲታረም አመልካች በቀን 18/05/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ክርክሩ በተጀመረበት ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ 1ኛተጠሪ ከሳሽ፣የአሁኑ አመልካች እና 2ኛተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበችዉ ክስ ንብረትነቱ የሚች እናቷ የሆነዉን ያልተከፋፈለ የዉርስ ሀብት 2ኛ ተጠሪ ራሱን ብቸኛ ወራሽ እንደሆነ አድርጎ የወራሽነት ማስረጃ ወሰዶ እና ስመሀብቱን ወደ

ራሱ በማዞር ለአመልካች በሽያጭ ዉል ማስተላለፉ የከሳሽን መብትና ጥቅም የሚነዳ ተግባር በመፈጸሙ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል በፍ/ብ/ህግ ቁጥር1696፣18704 እና 1706 መሰረት እንዲፈርስ የሚል ነዉ፡፡ተከሳሾች ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬነገር ክርክር በማንሳት የተከራከሩ መሆኑን፤በፍሬነገር ረገድ 2ኛ ተጠሪ የወራሽነት መብቱን በጊዜዉ ጠይቆ ባገኘዉ መብት መሰረት ቤቱን በሽያጭ ማስተላለፉን፤1ኛ ተጠሪ በወቅቱ መብቷን አለመጠየቋን፤ዉሉ ስርዓቱን ጠብቆ የተፈጸመ ስለሆነ የሚፈርስበት ምክንያት አለመኖሩን ገልጸ የተከራከረ መሆኑን፤አመልካች በበኩሉ በተጠሪዎች መካከል ያለዉን ዝምድና ግንኙነት የሚያዉቀዉ ነገር እንደሌለ፣የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገዛ ሰዉ ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ማለትም ንብረቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም መመዝገቡን፣ማንኛዉም የመንግስት እዳ እና እገዳ የሌለበት መሆኑንና በፍርድ ቤት የተሰጠዉን የዉርስ ዉሳኔ በመመልከት በአግባቡ አጣርቶ ግዥዉን የፈጸመ እና በዉልና ማስረጃ በማጸደቅ የገዛ መሆኑን ጠቅሶ ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መከራከሩን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሣያል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ ማድረጉን ጠቅሶ በስረ ነገር የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ክርክር የተነሳበት ቤት የሟች ወ/ሮ ሃዋ ሪራሽ የግል ንብረት ስለመሆኑ፤ሟች በህይወት እያሉ 1ኛተጠሪን፣ የ2ኛ ተጠሪ እናት(ወ/ሮ መርየም ነጋዬ) እና ሌሎች ተወላጆችን አፍረተዉ እንደነበር የተረጋገጠ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ሟች እናቱን ወራሽነት ካረጋገጠ በኋላ በተተኪ ወራሽነት የአያቱን የዉርስ ንብረት በማጣራት ለፍርድ ቤት ያቀረበዉ ሪፖርት በማጸደቅ በዚሁ መነሻ ስመ ሀብቱን ወደ ራሱ በማዞር በሽያጭ ማስተላለፉንና ስመ ሀብቱም ወደ ግዥ መዛወሩ የተረጋገጠ መሆኑን ነገር ግን የ2ኛ ተጠሪ እናት ከአያቱ በኋላ ስለሞቱ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 842(3) እና ሰበር መ/ቁ/110040 መሰረት ወላጅ እናቱን ተክቶ አያቱን ሊወርስ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ይህንኑ ተከትሎ በመ/ቁ/66899 የተሰጠዉ ወራሽነት ማስረጃም ሆነ ስመ ሀብቱ በስሙ የተዛወረበት አግባብ ከህግ ዉጭ ነዉ፤አመልካችም ሰነድ ብቻ በማየት ያደረገዉ ዉል ተገቢዉን ማጣራት ሳያደርግ መብት ከሌለዉ ሰዉ የገዛ በመሆኑ በቀን 16/02/2012ዓ.ም የተደረገዉ ሽያጭ ዉል ሊፈርስ ይገባል፤ ለአመልካች እና ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ እንዲሰረዝ እና ንብረቱ በወራሾች መካከል በዓይነት ወይም በገንዘብ ክፍፍል እንዲደረግ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡የአመልካች ጠበቃ በቀን 18/05/2014ዓ.ም ጽፎ ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፤ግዥ ንብረቱ በሻጩ ስም የተመዘገበ መሆኑን ተገቢዉን ማጣራት አድርጎ ከገዛ ሌሎች ወራሾች ገንዘቡን ከሻጩ መጠየቅ የሚችሉ ስለመሆኑ ሰበር ችሎት ዉሳኔ መስጠቱን፤አመልካችም የሰነዶቹን ህጋዊነት በማጣራት የገዛ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን፤ዉሉ ከመፈጸሙ በፊት ወደ ቦታዉ የላኩት ተወካይ ሳይኖር ተወካይ ማንነት እና ዉክልና መኖሩ ባልተለየበት በሀሰት የተሰጠ የምስክርነት ቃል አመልካች ይዞታዉ የማን እንደሆነ እያወቀ ገዝቷል መባሉ ስህተት መሆኑን፤ጎሬበት ናቸዉ የተባለዉንም በግልጽ በመካድ ተከራክረያለሁ፤ቤት ዉስጥ ሲትኖር የነበረችዉ የ2ኛ ተጠሪ እናት መሆኗን ምስክሮች ማስረዳታቸዉን፤ተተኪ ወራሽ በሚመለከት የስር ፍርድ ቤት የተሳሳተ የህግ ትርጉም መስጠቱን እና ባልተጠየቀ ዳኝነት መወሰኑ፤ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት ቢኖር የሻጩ ድርሻ ላይ ሊፈርስ የማይገባ መሆኑን በመዘርዘር እና የተለያዩ የሰበር ችሎት ዉሳኔ በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲታረም በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ንብረት 2ኛ ተጠሪ የዉርስ ንብረት እንዲጣራ በማድረግ በስር ፍርድ ቤት አጸድቆ በስሙ በማዛወር ለአሁኑ አመልካች በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ያስተላለፈዉን ስር ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የወሰነበትን አግባብነት ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/113529 እና መ/ቁ11772 በሆኑ መዝገቦች ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዟል፡፡

የ1ኛ ተጠሪ ጠበቃ በቀን 08/07/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ ተጠሪ ከሀገር ዉስጥ ያለመኖር እና ለህክምና ወደ ሌላ ቦታ መዘዋወሪን ተገን በማድረግ ህጋዊ መብት ከሌለዉ 2ኛ ተጠሪ መግዛታቸዉ ባለመብት አያደርጋቸዉም፤አመልካች በተጠሪዎች መካከል ዝምድና መኖሩን የማረጋጥ ሃላፊነት የሌለባቸዉ መሆኑን ከመግልጽ ያለፈ ጎሬበት አለመሆናቸዉን በመልሳቸዉ በግልጽ ያልካዱ መሆኑ የቅን ልቦና ግዥ ያለመሆናቸዉን፤ 2ኛ ተጠሪ ካርታ ያወጣዉ በሀሰት መሆኑን እና አከራካሪዉን ቤት አከራይቼ የምጠቀም መሆኑን በአካባቢ የሚታወቅ በመሆኑ ምክንያት አመልካች ቅን ልቦና ግዥ ባለመሆናቸዉ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔዎች ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የላቸዉም፤2ኛ ተጠሪ ቤቱን የመዉረስ መብት ሳይኖረዉ ያደረገዉ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡የ2ኛ ተጠሪ ጠበቃ በቀን 08/07/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ የዉርስ ሀብት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጣርቶ በፍርድ ቤት የጸደቀዉ በቀን 20/03/2010ዓ.ም መሆኑን፤ስመሀብቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበዉ በቀን 14/07/2010ዓ.ም መሆኑንና የሽያጭ ዉል ከሁለት ዓመት በኋላ በቀን 20/04/2012ዓ.ም የተፈጸመ መሆኑን በመጥቀስ በመመሳጠር የተፈጸመ ነዉ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ምንም ህጋዊም ሆነ የማስረጃ ምክንያት አልነበረም፤የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊታረም የሚገባ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸዉን ሲመስል እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የ1ኛ ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መሰረቱ የተሸጠዉ ቤት ሌሎች ወራሾች መብት ያለበት ሆኖ እያለ 2ኛ ተጠሪ ራሱን ብቸኛ ወራሽ አድርጎ ማስረጃ ወስዶ ለአመልካች በሽያጭ ቤቱን ማስተላላፉ መብትና ጥቅሟን የሚጎዳ ስለሆነ ዉሉ እንዲፈርስ በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ አንድ ዉል እንዲፈርስ የሚደረገዉ ዉሉ የተቋቋመበት ሁኔታ ከመሰረቱ ግድፈት ሲኖርበት ነዉ፡፡ይኸዉም ለዉል ምስረታ የሚያስፈልጉ የችሎታ ወይም ፈቃድ ጉድለት ሲኖር ወይም የዉለታዉ ጉዳይ ህግን ወይም ግብረ ገብነት/ሞራል/ የሚጻረር ሲሆን ወይም በህግ የተደነገገዉን ፎርም ሳያሟላ ሲቀር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላ ሁኔታ ዉሉ ጉድለት አለበት በሚል ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚችለዉ ወገን ማንነት እንደየምክንያቱ የሚለያይ መሆኑም በዚሁ ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል፡፡ዉሉ የተደረገበት ሁኔታ ችሎታ ወይም የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚል የሚነሳዉ ክርክር በተዋዋይ ወገኖች በኩል የሚቀርብ እንደሆነ እና የወሉታዉ ጉዳይ ህጋዊነት ወይም የአደራረግ ስርዓት ጉድለት በማናቸዉም ጥቅም ያለዉ ሰዉ ሊነሳ የሚችል ነዉ፡፡

በዚህ ጉዳይ የቤት የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የተወሰነበትን ምክንያት አመልካቹ ተገቢዉን ማጣራት አላደረገም የተባለበት ሁኔታ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በቀዳሚነት መርምረናል፡፡በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ የገዛ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ነዉ፡፡መዝገቡ እንደሚያሣየዉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ንብረት 2ኛ ተጠሪ የዉርስ ንብረት እንዲጣራ በማድረግ በስር ፍርድ ቤት አጸድቆ በስሙ በማዛወር ለአሁኑ አመልካች በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተደረገ የቤት

ሽያጭ ዉል ያስተላለፈ መሆኑ እና ስመ ሀብቱም ወደ አመልካች የተላለፈ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የተነሳ ህጉ ልዩ ጥበቃ ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ መብት ማቋቋም ወይም ማስተላለፍ የሚመለከቱ ህጋዊያን ተግባራት ሁሉ በጽሁፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግ አለበት የሚለዉ የህግ አሰገዳጅ ድንጋጌ ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ይመለከታል፡፡ከዚህም ባሻገር የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚገኝበት አስተዳደር ክፍል መዝገብ ዉስጥ ተመዝግቦ እንዲገኝ ህጉ ግድ ይላል፡፡የፍ/ብ ህግ ቁ/1567 እና 1570፣1645 እና 2878 ይመለከታል፡፡የዚህም ምዝገባ አስፈላጊነት በማናቸዉም ሁኔታ በንብረቱ ላይ ለተቋቀቋመ መብት ዋስትና ማረጋገጥ ብሎም መብት ለማስተላለፍ ወይም ለማቋቋም የሚሹ ሶስተኛ ወገኖች ይህንኑ አዉቀዉ ለመዋዋል እንዲችሉ ለማድረግ እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲደረግ የማድረጉ አስፈሊጊነት በተዋዋይ ወገኖቹ መካከል የፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ዓላማ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረዉ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡በሌላ አገላለጽ የማይቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል በንብረት ምዘገባ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ የሚደረግበት ዋነኛዉ ምክንያት ሶስተኛ ወገኖች ይህንኑ አዉቀዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነዉ፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195 ላይ እንደተደነገገዉ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ሀብት በስሙ የተመዘገበ ሰዉ የዚሁ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ የህግ ግምት ይወሰዳል፡፡ንብረቱ በስሙ የተመዘገበ ሰዉ ይህንኑ ንብረት የመሸጥ ወይም በሌላ አግባብ የማስተላለፍ ሙሉ መብት ያለዉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1205 ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡ የማይንቃሳቀስ ንብረት ገዥም ስመ ንብረቱ በሻጭ የተመዘገበና ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን ከሚመለከተዉ አስተዳደር አካል በማረጋገጥ የተዋዋለ እንደሆነ አንድ ጠንቃቃ ሰዉ ማድረግ የሚጠበቅበት ጥንቃቄ እንዳደረገ ግምት ተወስዶ ሕጉ ጥበቃ ያደርግለታል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1553 እስከ 1646፣2878 እና 3052 ድንጋጌዎች የማይንቀሰቃስ ንብረት ምዝገባ አስፈላጊነትም የንብረት መብት ጥበቃ ለማረጋገጥ፣የግብይት ዋስትና እና የ3ኛ ወገኖችን መብት ለማስከበር እንደሆነ የሚያሥገነዝቡ ናቸዉ፡፡ስለዚህም የማይንቃሳቀስ ንብረት ላይ በዉል መብት ለማቋቋም የፈለገ ሰዉ እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ይህንኑ ስርዓት ተከትሎ ማለትም ስመ ንብረቱ በሻጭ ስም የተመዘገበና ንብረቱ ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡በዚህ ረገድ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረጉ ከተረጋገጠ ዉሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2881 ይመለከታል፡፡

2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ለአመልካች የሸጠዉ የሌሎች ወራሾችን ስምምነት አግኝቶ ባይሆንም የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ እና የቤቱን ስመ-ሀብት ከሸያጩ ዓመት በፊት ከተገቢው የአስተዳዳር አካል ካገኘ በኋላ መሆኑ፤ሸያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነው፡፡ይህንኑ በማጣራት ዉል ያደረገ ገዥ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጓል ተብሎ በህግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለሆነ አመልካች ተገቢዉን ጥንቃቄ አላደረገም የሚያሰኝ ምክንያት የለም፡፡በሌላ የፍሬነገር ከርክር የነበረዉ ከአመልካቹ ጎሬበት ስለሚገኝ ቤቱ በትክክል የ2ኛ ተጠሪ መሆን አለመሆኑን የማጣራት እድል ነበረዉ የሚለዉን በተመለከተ አመልካች ጎሬቤት መሆኑን አልካደም በሚል መነሻ የስር ፍርድም ንብረቱ የግል መሆን አለመሆኑን ማጣራት እድል ነበረዉ የሚል ግምት መዉሰዱን ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት ማየት እንደሚቻለዉ ወ/ሮ ሃዋ ከሞተች በኋላ ቤቱ ዉስጥ ስትኖር የነበረችዉ የ1ኛ ተጠሪ እናት እንደሆነች ነዉ፡፡በሌላ በኩል ግቢዉን ለተሸከርካሪ ማቆሚያ 1ኛ ተጠሪ አከራይታ ትጠቀም ነበር ከመባሉ ዉጪ ተጠሪዋ በዚህ ቤት ሲትኖር እንዳልነበር ራሷም በግልጽ ያመነችዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቹ ቤቱ የሌላ ሰዉ መሆኑን እያወቀ በክፉ ልቦና ያደረገዉ ዉል ነዉ ለማለት የሚያስችል ፍሬነገር መኖሩን አያሣይም፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የቤቱ አመጣጥ የዉርስ ቢሆንም ከአመልካቹ አኳያ ሲታይ ሆነ ብሎ ከሻጩ ጋር በመመሳጠር የፈጸመዉ ተግባር መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር ጎሬበት በመሆኑ ብቻ ማወቅ ነበረበት ብሎ ግምት መዉሰድ የሚቻልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ስለዚህም የማይንቀሳቀስ ንብረት ገዥ በዋናነት እንዲያጣራ የሚጠበቀዉ የምዝገባ ስርዓቱን በመሆኑን እና በአመልካች በኩል በተንኮል ወይም በመመሳጠር የተፈጸመ ተግባር በሌለበት አመልካች ተገቢዉን ማጣራት አላደረገም የሚለዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ምክንያት የህግም ሆነ የፍሬነገር መሰረት የለዉም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ቤቱን ያለ እነሱ ፈቃድ የተሸጠባቸዉ ወራሾች የሚኖራቸዉ መብት ዉሉን ማስፈረስ ሳይሆን ከሌላኛዉ ወራሽ መብታቸዉን መጠየቅ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ያሣያል፡፡በሰበር ችሎቱ ዉሳኔ እንደተገለጸዉ ከወራሾች አንዱ ወራሽነቱን አረጋግጦ የዉርስ ንብረቱን ስመ ሀብት ወደ ራሱ ካዞረ በኋላ በሽያጭ ለሶስተኛ ወገን ያሥተላለፈ እንደሆነ ሌሎች ወራሾች የሚኖራቸዉ መብት ከሻጩ ላይ የዉርስ ድርሻቸዉን መጠየቅ እንጂ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛዉን የሶስተኛ ወገን የሽያጭ ዉል የማስፈረስ መብት አይኖራቸዉን የሚል ነዉ፡፡የሰበር መ/ቁ/45370፣46527 እና 47378 (ቅጽ 10 ላይ የታተመ) እና ሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦችን ይመለከታል፡፡የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ

አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት እንደሚኖረዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26/3/ ስር ተደንግጓል፡፡

ሌላዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ምክንያት የ2ኛ ተጠሪ እናት የሞተችዉ ከአያቱ በኋላ ስለሆነ ተተኪ ወራሽ ሊሆን አይችልም በማለት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 842(3) በመጥቀስ ነዉ፡፡በመሰረቱ 1ኛ ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀችዉ 2ኛ ተጠሪ ሌሎች ወራሾች መኖራቸዉን እያወቀ ራሱን ብቸኛ ወራሽ አድርጎ የወራሽነት ማስረጃ መዉሰዱ መብትና ጥቅሟን ለመጉዳት አስቦ ነዉ በሚል እንጂ የአያቱ ንብረት ላይ የወራሽነት መብት የለዉም በሚል ምክንያት አለመሆኑን ከመዝገቡ ተገንዝበነናል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ 2ኛ ተጠሪ በተተኪነት መዉረስ መቻል አለመቻል ጉዳይ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ ዉሳኔ መስጠቱን ያሣያል፡፡ይህም ባልተጠየቀ ዳኝነት ከመሆኑም አኳያ ሲታይ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 182(2) ድንጋጌ የሚጣረስ ስለሆነ አግባብነት የለዉም፡፡ከዚህም ባሻገር የ2ኛ ተጠሪ እናት የሞተችዉ ከወላጅ እናቷ በኋላ መሆኑም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 842(3) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የተተኪ ወራሽነት መብት ጥያቄ የሚነሳዉ የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆነዉ ልጅ ከአዉራሹ ቀድሞ ቢሞት የእሱ ልጅ የሆነዉ ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅ በተተኪነት የሚያገኝበት ሁኔታ ነዉ፡፡ነገር ግን የሟቹ ልጅ ከአዉራሹ በኋላ የሞተ እንደሆነ በህግ ወርሶ እንደሞተ ስለሚገመት ድርሻዉን የሚያገኝበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህግቁጥር 833 ተደንግጓል፡፡በዚህ ረገድ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ ዉሳኔ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 113529 የሰጠዉ ዉሳኔ (በቅጽ 20 ላይ የታተመዉ) ነዉ፡፡ሰበር ችሎቱ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ከተመለከተዉ በተመሳሳይ ሁኔታ የ2ኛ ተጠሪ አያቱ በሞቱበት ጊዜ እናቱ በህይወት ስለነበሩ እና ወራሽነት አይገባቸዉም ስላልተባለ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 830 ድንጋጌ መሰረት እና የእናቱን ድርሻ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት መብት ያገኛል፡፡ከዚህም የምንገዘበዉ 2ኛ ተጠሪ ከአያቱ ንብረት ላይ በእናቱ ድርሻ ልክ የማግኘት መብት ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ከአያቱ ንብረት ላይ መዉረስ መብት የለዉም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢነት የለዉም፡፡በጥቅሉ ሲታይ የወራሽነት መብት እና ድርሻ ጉዳይ በወራሾች መካከል በሚደረግ ክርክር የሚወሰን መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ሀበቱ በህግ አግባብ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑን እና ከእዳ እና እገዳ ነጻ መሆኑን በማጣራት እና ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት የተደረገ መሆኑ በመረጋገጡ የሽያጭ ዉል የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም ዉሉ እንዲፈርስ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች

የተሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪን ጨምሮ ሌሎች ወራሾች መብታቸዉን ከሻጩ ላይ ከሚጠይቁ በስተቀር በህግ አግባብ የተደረገዉን ዉል ማፍረስ አይገባም የሚለዉን የሰበር ችሎቱን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ2(4/ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁአግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/18642 ላይ በቀን 30/05/2014ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ ተሸሯል፡፡

2ኛ/ክርክር የተነሳበት ቤት ላይ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 20/04/2012ዓ.ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል የሚፈርስበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

2ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ14/06/2014ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 220204
ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች ፡- 1. አቶ ታምሩ በዜ

2. አቶ ዘዉዱ ከበደ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ በዜ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ዉል ለማስፈረስ በቀረበ ክስ መነሻ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ ተጠሪ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ ከ1ኛ አመልካች ጋር የጋራ እናታቸዉ የሆኑት ሟች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ ያፈሩት በደብረ ሲና ከተማ ዉስጥ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉ የቦታ ቁጥሩ 122 የሆነ መኖሪያ ቤት ነበራት፤ከ1ኛ አመልካች ጋር የሟች እናታችን ወራሽ መሆናችንን አረጋግጠናል፡፡ተጠሪና 1ኛ አመልካች በጋራ እያስተዳደርን ፣እያከራየንና በወለድ አግድ በማስያዝ በገንዘቡ ስንጠቀም ቆይተናል፡፡ይህንን ከ1ኛ አመልካች ጋር የጋራ የዉርስ ሀብታችን የሆነዉን እኔ ሳላዉቅ እንዲሁም ፈቃደን ሳልገልጽ 1ኛ አመልካች ለ2ኛ አመልካች ሸጠዋል፡፡ 2ኛ አመልካችም ጎረቤት በመሆናቸዉ

በቤቱ ላይ ተጠሪ የዉርስ ድርሻ እንዳላቸዉ እያወቁ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ አግባብ ቤቱን መግዛታቸዉን ገልጸዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስና ድርሻቸዉ በአይነት ተካፍሎ እንዲሰጣቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የሚች እናታችን ሳይሆን የ1ኛ አመልካች አባት የሆኑት የአቶ በዜ ሳህሉ የግል ንብረት ሆኖ ከሌሎች ከሚች አቶ በዜ ሳህሉ ወራሾች ጋር የንብረት ክፍፍል ተደርጎ ለ1ኛ አመልካች የደረሰኝ የግል ንብረቴ ነዉ፡፡ሚች እናታችን የሚች አባቴ ሚስት እንደሆኑና የሚስትነት ድርሻ ይገባኛል በማለት ተከራክረዉ ሚስት እንዳልሆኑ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም፡፡ ክስ የማቅረብ መብታቸዉም በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች አቅርበዋል፡፡ እንዲሁም ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ ተጠሪ የዉርስ ድርሻ እንደሌላቸዉ፤ቤቱ የ1ኛ አመልካች ሀብት እንደሆነ፤ ከቀን 20/02/1990 ዓ/ም ጀምሮ በእጄ አድርጌ የባለይዞታነት ማረጋገጫ አዉጥቼ የምጠቀምበት ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪም ቤቱ የአመልካች ሀብት መሆኑን 1ኛ አመልካች ከአቀረቡት የይዞታ ማረጋጫ አረጋግጠዉ ግዥ እንደፈጸሙ በመግለጽ ዉሉን ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት የለም ተብሎ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አስቀድሞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ዉድቅ በማድረግ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን ሰምቶ በመ/ቁጥር 0136997 ላይ በቀን 18/10/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የ1ኛ አመልካችና የተጠሪ እናት የሚች አቶ በዜ ሚስት አይደሉም ተብሎ መወሰኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በትዳር አብረዉ መኖራቸዉ እና የ1ኛ አመልካች አባት ቤቱን ለቆላቸዉ በአከራካሪዉ ቤት ዉስጥ ሆነዉ የተጠሪ እናት ልጅ ያሳድጉ እንደነበር ተመስክሯል፡፡ቤቱን በጋራ ባታፈራ ኖሮ ይህ አይሆንም ነበር፡፡አስቀድሞ የተሰጠዉ ዉሳኔ ቤቱ የጋራ ነዉ ወይስ አይደለም በሚል ጭብጥ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ አይደለም፡፡በወለድ አግድ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ቤቱን አስይዘዉ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ቤቱ ለተጠሪ ጭምር በዉርስ የተላለፈ የጋራ የዉርስ ሀብት ነዉ፡፡ 1ኛ አመልካች ቤቱን ለ2ኛ አመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት ተጠሪ ሳይፈቅዱና በተጠሪ የተሰጣቸዉ ዉክልና ሳይኖር እንደሆነ ማረጋገጡን ገልጾ የጋራ የሆነዉን ንብረት አንደኛዉ ወገን ብቻ የሌላዉን ድርሻ አካቶ መሸጥ ስለማይችል በአመልካቾች መካከል በቀን 12/03/2012ዓ/ም የተደረገዉ የሽያጭ ዉል ፈራሽ ነዉ፤ቤትና ቦታዉ ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ የጋራ ሀብት ስለሆነ በዉሳኔዉ ላይ በተመለከተዉ አግባብ 1ኛ አመልካችና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ላይ አለኝ የሚሉትን ገንዘብ ከመጠየቅ ዉሳኔዉ አያግዳቸዉም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 01-21616 ላይ በቀን 30/03/2014 ዓ/ም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ትእዛዝ ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካቾች በቀን 24/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ወ/ሮ አመለ ቦጋለ እና አቶ በዜ ሳህሌ ባልና

ሚስት እንዳልነበሩና የጋራ ሀብት እንዳላፈሩ በማስረጃ አስረድተናል፡፡ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ ተጠሪ የዉርስ ድርሻ የላቸዉም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 1ኛ አመልካች ከወላጅ አባቱ በዉርስ ተላልፎልኝ በስሜ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር አዉጥቸበት በስሜ ግብር እየከፈልኩ ስጠቀምበት የቆየሁት ቤት ነዉ፡፡እናታችን የ1ኛ አመልካች ሚስት ካልሆኑ ባለቤታ ካልሆነ ሰዉ ጋር የጋራ ንብረት የምትካፈልበት አግባብ ባለመኖሩ ክስ የቀረበበትም ቤት ለሟች አመለ ቦጋለ የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ የክፍፍል ሰነድ በሌለበት የግል ሀብታቸዉ ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡1ኛ አመልካች በሕጋዊ መንገድ ቤቱን በሽያጭ ለ2ኛ አመልካች አስተላልፈዉያለሁ፡፡እንዲሁም 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በ1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና እግድ እንደሌለበት አረጋግጫለዉ የቤት ሽያጭ ዉሉን በቅን ልቦና ከአመልካች ጋር ተዋዉዬ የገዛሁት ነዉ፡፡ ቤቱ የጋራ ነዉ ከተባለም ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ዉክልና ሳይሰጡ ቤቱን 1ኛ አመልካች ሸጠዋል የሚባል ከሆነም በሰ/መ/ቁጥር 47373፣46527 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የሽያጭ ዉሉን ከማፍረስ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ተጠሪ ድርሻቸዉን ከ1ኛ አመልካች እንዲጠይቁ መወሰን ሲገባዉ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጠሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ በሰጠዉ ትእዛዝ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ መወሰኑንና የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ የተወሰነበትን አግባብ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 28/10/2014ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ተጠሪ ወላጅ እናት ከአቶ በዜ ሳህሌ ተካፍላ የደረሳት ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡ሟች እናታችን ከሞተች በኋላ 1ኛ አመልካችና ተጠሪ በጋራ በአንድነት ወራሽነታችን አሳዉጀን ይህንን ቤት ይዘን በወለድ አግድ ጭምር አስይዘን ስንጠቀም እንደነበር ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያለዉ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡1ኛ አመልካችና ተጠሪ ወራሽነታችንን በጋራ አረጋግጠናል፡፡የጋራ ንብረት ሊገኝ የሚችለዉ በጋብቻ ብቻ ሳይሆን እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ወይም ከዚህ ግንኙነት ዉጭ በሆነ ሁኔታ ቤቱን በጋራ በመስራትና በማፍራት ወይም በሌሎች መንገዶችም ሊሆን ይችላል፡፡ሟች እናቴ የሟች አቶ በዜ ሳህሉ ሚስት አይደለችም ተብሎ መወሰኑ በጋራ አላፈሩትም ወይም በስምምነት ተካፍለዉ ይህ ቤት አልደረሳቸዉም የሚያስብል አይደለም፡፡ ለ1ኛ አመልካች እና ለተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ ተረጋግጦ ያለተጠሪ ፈቃድ የተፈጸመዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል የተመዘገበዉ የክርክሩን አመጣጥና የግራ ቀኝ ክርክር በአጭሩ የሚያሳይ ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም የሚችል ስህተት በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክሱን የመሰረቱት ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ የጋራ እናት የሆኑት በህይወት ባሉበት ጊዜ ያፈሩትን በክሱ የተጠቀሰ ቤት ለመዉረስ ከአመልካች ጋር በጋራ

ወራሽነታቸዉን አረጋግጠዉ ሲጠቀሙ ቢቆዩም 1ኛ አመልካች ያለእርሳቸዉ ፈቃድ ለ2ኛ አመልካች በሽያጭ ማስተላለፋቸዉ፤ እንዲሁም 2ኛ አመልካችም ጎረቤት ስለሆኑ ቤቱ የጋራ ሀብት መሆኑን እያወቁ ከቅን ልቦና ዉጭ የቤት ሽያጭ ዉሉን ስለፈጸሙ ዉሉ ፈርሶ ድርሻዬ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡1ኛ አመልካች ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የአባታቸዉ የሟች አቶ በዜ ሳህሉ ሀብት እንጂ የእሳቸዉና የተጠሪ እናት የጋራ ሀብት እንዳልሆነና የተጠሪ እናት የሟች አቶ በዜ ሳህሉ ሚስት እንዳልሆኑ እንዲሁም ቤቱ በስማቸዉ ዞሮ ከተመዘገበ በኋላ በሽያጭ ለ2ኛ አመልካች ያስተላለፉት እንደሆነ በመግለጽ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡2ኛ አመልካችም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የ1ኛ አመልካች የግል ሀብት መሆኑን ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ መግዛታቸዉን በመግለጽ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት የ1ኛ አመልካችና የተጠሪ እናት የ1ኛ አመልካች አባት ሚስት እንዳልሆኑ አስቀድሞ በፍርድ መወሰኑን 1ኛ አመልካች ባቀረቡት ማስረጃ ቢረጋገጥም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የ1ኛ አመልካችና የተጠሪ እናት እና የ1ኛ አመልካች አባት በጋራ ያፈሩት እና በኋላም ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ እናት የደረሳቸዉ ድርሻ እንደሆነና በዉርስ ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ የተላለፈ ሆኖ እያለ 1ኛ አመልካች ብቻቸዉን በሽያጭ ለ2ኛ አመልካች ማስተላለፋቸዉ ዉሉን ፈራሽ ያደርገዋል በማለት በአመልካቾች መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ ወስኗል፡፡

ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 1ኛ አመልካች በሽያጭ ለ2ኛ አመልካች ያስተላለፉት የቤቱ ስመ ሀብት በስማቸዉ ዞሮ ከተመዘገበ በኋላ ነዉ፡፡1ኛ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይም ክስ የቀረበበትን ቤት ለ2ኛ አመልካች ከመሸጣቸዉ በፊት በስማቸዉ ግብር እየገበሩና በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወስደዉ ሲያስተዳድሩ እንደነበር የገለጹትን ተጠሪ ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ይህም የሚያሳየዉ 1ኛ አመልካች አከራከሪዉን ቤት ለ2ኛ አመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት ከሽያጩ በፊት የቤቱ ስመ ሀብት በስማቸዉ ከተመዘገበ በኋላ መሆኑን ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘዉ ሰዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡አንድ ሰዉ በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገድ ለሌላ ሰዉ የማስተላለፍ መብት ስለአለዉ ንብረቱ በስሙ መመዝገቡን የሚያሳይ ማስረጃ የያዘ ሰዉ በስሙ የተመዘገበዉን ንብረት ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በዚህ መሰረት 1ኛ አመልካች በስማቸዉ የአከራካሪዉ ቤት ባለሃብትነት ምስክር ወረቀት መያዛቸዉ ንብረቱ የግል ሀብት እንደሆነ የሚያስቆጥር ሲሆን ይህንን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን የሚገዛ ሰዉ ሽያጩን ከሕግ አግባብ ዉጭ አከናዉኗል የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

እንዲሁም ተጠሪ ክሱን ሲያቀርቡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለ1ኛ አመልካችና ለተጠሪ የጋራ እናታቸዉ የሆኑት ሟች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ በህይወት እያሉ ያፈሩት የግል ሀብታቸዉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት ደግሞ በአንድ በኩል ሟች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ የሟች አቶ በዜ ሳህሌ ሚስት እንዳልነበሩ በፍርድ እንደተወሰነ የሚያሳይ ማስረጃ እንደቀረበ እየገለጸ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱን የ1ኛ አመልካች አባት ሟች አቶ በዜ ሳህሌ ለቆላቸዉ ሟች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ ይዘዉ ስለቆዩ ቤቱን ሟች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ ከሟች በዜ ሳህሌ

ጋር በጋራ ባያፈሩት ኖሮ ቤቱ ሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ ይዞታ ስር ሊገባ አይችልም ነበር፡፡ስለሆነም አከራካሪው ቤት የሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ ንብረት ነዉ፡፡ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ የደረሰበት ድምዳሜ በግምት ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በተጨማሪ የሕግ መሰረት ያለዉ አይደለም፡፡ምክንያቱም ሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ የሚች አቶ በዜ ሳህሌ ሚስት ካልነበሩ የንብረት ክፍፍል ተደርጎ የሚስትነት ድርሻ አግኝተዋል ሊባል የሚችለበት የሕግ አግባብ ካለመኖሩም በተጨማሪ ተጠሪም ክሳቸዉን በዚህ አግባብ አላቀረቡም፡፡የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንብረት ክፍፍል ተደርጎ ይህ ቤት ለሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ የደረሳቸዉ ስለመሆኑም በማስረጃ አረጋግጦ የደረሰበት ድምዳሜ አይደለም፡፡እንዲሁም ሚች አቶ በዜ ሳህለ እና ሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ የባልና ሚስት ግንኙነት በመካከላቸዉ ሳይኖር ንብረት በጋራ አፍርተዉ በጋራ ያፈሩትንም ንብረት ተከፋፍለዉ ይህ አከራካሪዉ ቤት ለሚች ወ/ሮ አመለ ቦጋለ የደረሳቸዉ ድርሻ እንደሆነና በዉርስ ለ1ኛ አመልካች እና ለተጠሪ የደረሳቸዉ ስለመሆኑ ተገልጾ የቀረበ የክስ ፍሬ ነገር በሌለበት የስር ፍርድ ቤት ከላይ በተገለጸዉ ድምዳሜ ላይ መድረሱ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ ከመሆኑም በተጨማሪ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል 1ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለ2ኛ አመልካች የሸጡት በስማቸዉ ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት በመሆኑ ቤቱን ለመሸጥ የተጠሪን ፈቃድ ለመጠየቅ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ 2ኛ አመልካችም ቤቱን የገዙት አከራካሪዉ ቤት በ1ኛ አመልካች ስም የተመዘገበ የግል ንብረታቸዉ መሆኑን በማረጋገጥ በመሆኑ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ግዥ ፈጽመዋል የሚያስብል ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት 1ኛ አመልካች ለ2ኛ አመልካች በሽያጭ ለማስተላለፍ በቀን 12/03/2012ዓ/ም ያደረጉትን ዉል የሚያስፈርስ ምክንያት በሌለበት ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 0136997 ላይ በቀን 18/10/2013ዓ/ም የሠጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-21616 ላይ በቀን 30/03/2014 የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. በአመልካቾች መካከል የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል የሚያስፈርስ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡

2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል፤ይጸፍ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 220031

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ሽፋ ኢብራሂም ፡- ጠበቃ አብዱራዚት ረሽድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- በሻዱ ቱፋ ዋንታሎ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.281388 በቀን 20/04/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር ዞን 2 ወረዳ 24 ቀበሌ 17 በአሁኑ አጠራር ክ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ ነዋሪ ሲሆን ይህንን ይዞታዬን ከ1969 ዓ.ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጀምሮ ይገፀው በእርሻ ስራ እየተጠቀምኩበት የምገኝ አርሶ አደር ስሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በ2010 ዓም ባወጣው መመሪያ መሰረት በወረዳው የገበሬዎች ኮሚቴ፣ በወረዳው ግብርና አርሶ አደር ልማት ጽ/ቤት እና በወረዳው ካቢኔ ይዞታዬ ተለክቶ 3324 ካሜ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ አስ/ጽ/ቤት/ለስር 4ኛ ተከሳሽ/ ተልኮለት ካርታ ሰርቶ መስጠት ሲገባው ካሳ ሳይከፈለኝና ምትክ ቦታ ሳይሰጠኝ አመልካች እና ለስር 2ኛ ተከሳሽ በይዞታዬ ላይ ካርታ ሰርቶ ሰጥቷል፡፡ የስር 3ኛ ተከሳሽ የግንባታ ፈቃድ በመስጠት የአሁን አመልካች ይዞታዬን ነጥቀው በውስጡ የዕቃ ማስቀመጫ ስቶር እና አጥር በመስራት የሁከት ተግባር ጥር 28 ቀን 2013 ዓም የፈጠሩብኝ ስለሆነ የሁከት ተግባር እንዲወገድልኝ፣ካርታውና የግንባታ ፈቃዱ እንዲመክንልኝ እና የተሰራው ስቶርና አጥር እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስም አከራካሪው ይዞታዬ የተሰጠኝ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማት ተነሺ ስለሆንኩ ባለቤት እንደሌለው እና ይዞታው የመንግስት ባዶ ቦታ መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ የሚጠይቁት መብትና ጥቅም ካለ ይዞታውን የሰጠኝን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ከሚጠይቁ በስተቀር አመልካችን የሚጠይቁበት አግባብ የለም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪ ይዞታውን በይዞታቸው ስር አድርገውት የማያውቁ ለእርሻ አገልግሎትም ውሎ የማያውቅ በመሆኑ የይዞታውን አዋሳኝ ሲገልፁም በደቡብ በኩል መንገድ ያዋስነዋል ብለው መግለፃቸው ይዞታውን ይዘው የማያውቁ መሆኑን ስለሚያሳይ፣አመልካች በይዞታው ላይ ካርታ ያለኝ በመሆኑ በይዞታው ላይ የተሻለ መብት እንዳለኝ ስለሚያሳይ አያስከስስም ተብሎ መዝገቡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.231(1)(ሀ) መሰረት ሊዘጋ ይገባል፣ይዞታው ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ በመሆኑ ከእጃቸው በወጣ ንብረት ላይ የመፋለም ክስ ከሚያቀርቡ በስተቀር ጥያቄው በሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊስተናገድ ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም አከራካሪው ይዞታ ከሀያ አመት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተያዙ የማህበር ይዞታዎች መካከል አንዱ ሲሆን በኋላም ለልማት ተነሺዎች መሰጠት ተጀምሮ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ውስጥ የሚገኘው መኖሪያ ቤቴ በመልሶ ማልማት ስለፈረሰ አስተዳደሩ ከስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ጋር በመነጋገር ቦታው ባዶ ቦታ መሆኑን ከ6 ወር በላይ አጥንቶ በምትክነት የሰጠኝ በመሆኑ በይዞታው ላይ ግንባታ ያከናወንኩትም ተገቢውን የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ በከተማው መሪ ፕላን መሰረት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስር ተከሳሾች ያቀረቡትን ክርክር በመስማትና ከሚመለከተው አካል ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጎ በሰጠው ውሳኔም የወረዳ አስተዳደሩ አርሶ አደር ኮሚቴ ተጠሪ ህጋዊ ባለይዞታ መሆናቸውን ከመግለፁ በተጨማሪ ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ/መ/ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት ደብዳቤ የላከ እና ይዞታውን በሚመለከት መብት ሊፈጠርላቸው ሂደት ላይ ሆኖ እያለ፣ለተጠሪ ምትክ ቦታ ወይም የካሳ ክፍያ ሳያዘጋጅ ወይንም የተጀመረውን የስነ ስርዓት ሂደት በመጠበቅ መብት

ሳይፈጥርላቸው ለአመልካችና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ማስተላለፉ ህገ ወጥ እና ሁከት ተግባር መሆኑን፤ የወረዳው አርሶ አደር ኮሚቴ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር 4ኛ ተከሳሽም ሆነ የሚመለከተው አካል አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፤አመልካችንና የስር 2ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ባቀረቡት ማስረጃ አማካኝነት መብት የተፈጠረላቸው በመሆኑ ህጋዊ መብታቸውን በመመሪያና ደንብ መሰረት በመጠበቅ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፤ስለሆነም አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት በሚገባው ጉዳይ በቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ባለይዞታው ማን እንደሆነ ሊወሰን የማይገባ በመሆኑ በይዞታው ላይ 4ኛ ተከሳሽ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በህጋዊ መንገድ የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ መብታቸውን በመጠበቅ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ሀተታው ላይ በግልጽ አከራካሪው ይዞታ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከሚሰጥበት በቀር ይዞታው የማነው የሚለው ሊወሰን እንደማይገባ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰውም የወረዳው አርሶ አደር ኮሚቴ ለተጠሪ ከፃፈላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ውጭ ከአመልካች እኩል የሚቆም ማስረጃ ስለሌላቸውም መሆኑን በሀተታው ተካትቷል፡፡ነገር ግን ከዚህ ፍፁም ተቃራኒ በሆነ መንገድ የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተራ ቁጥር 1 ላይ የከተማው አስተዳደር ተጠሪ በቦታው ላይ መብት እያላቸው ለአመልካች ማስተላለፉ የሁከት ተግባር ነው በማለት እርስ በእርሱ የሚጋጭ ተገቢነት የሌለው ውሳኔ ሰጥቶብናል፡፡ፍርድ ቤቱ ሁከት አለ ብሎ ሲያበቃ የስር 4ኛ ተከሳሽ ተጠሪን ጨምሮ ጉዳዩን በአስተዳደራዊ መንገድ መፍትሔ እንዲሰጥበት በመወሰን ጉዳዩን የበለጠ እርስ በእርሱ የሚጋጭ አድርጎብናል፡፡

ከመነሻው የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ገና ሙሉ በሙሉ መብት ስላልተቋቋመላቸው ቦታው የማነው የሚለውን ለመወሰን የማይቻል መሆኑን ካመነበት ሕጋዊ ካርታ ላለን ለአመልካች መወሰን ወይም በቂ ማስረጃ አልቀረበም ብሎ መዝጋት ይችላል፡፡የስር ፍርድ ቤት በተቃራኒው የሰጠው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ውሳኔ የአመልካችን መብት በእጅጉ ጎድቶታል፡፡የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ጉዳይ በአግባቡ ሳይመረምረው ይግባኙ አያስቀርብም ማለቱ መሰረታዊ ሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ብይን ባቀረብነው የሰበር አቤቱታ መሰረት ሙሉ በሙሉ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲታይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የተፈጠረው ሁከት ይቁም ሲል ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሆን አለመሆን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ በሰጡት መልስም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአስተዳደር ይታይ ያለው ከተፈጠረው የሁከት ተግባር አኳያ ሳይሆን አመልካች በአስተዳደር ጠይቆ እንዲወስድና ጉዳዩ በአስተዳደር እልባት የሚያገኝ ነው አለ እንጂ ተጠሪ በመመሪያ ቁጥር 20/2013 መሰረት እንዲሁም

መመሪያውን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2013 በቀን 01/02/2014 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 9(16) አርሶ አደሩ በማንኛውም ጊዜ ያለ አግባብ መሬቱ ለሌላ ሰው ተላልፎብኛል ብሎ ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ተጣርቶ ውሳኔ ሲሰጠው ቀደም ሲል በአርሶ አደር መሬት ላይ የተሰጠው ካርታ መክኖ መሬቱ ለአርሶ አደሩ ይመለሳል ብሎ የወጣ መመሪያ በመፃረር የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጠሪን ይዞታ ሳያሳውቁኝ ካሳና ምትክ ቦታ ሳይሰጡኝ ካርታ መስጠቱና አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ግንባታ ለመገንባት መንቀሳቀሱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1140-1149(1) መሰረት መወሰኑ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ውሳኔው እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡የሁከት ይወገድልኝ ክስ እና የባለሃብትነት ክስ ሁለቱም ከንብረት መብት የሚመነጩ ቢሆኑም ከክርክሩ አድማስ እና በፍሬ ነገር ደረጃ ተከራካሪዎች ሊያረጋግጡት ከሚገባው መሰረታዊ ጭብጥ አኳያ የተለያየ መነሻ እና ውጤት ያላቸው ህጋዊ መብቶች ናቸው፡፡ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን በተመለከተ በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች ውስጥ አንዱ በሀብቱ ላይ የተፈጠረው ህገ ወጥ ሁከት እንዲወገድለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ በቀረበ ክስ ላይ ሁከት ተፈጥሯል ተብሎ ውሳኔ የሚሰጠውም የተከሰሰው ሰው የሌላ ሰው ይዞታ መያዙ አልያም በይዞታው ላይ ሁከት መፍጠሩ ሲረጋገጥ እና የሁከት ክስ የቀረበበት አካልም የሥራውን አደራረግ የሚፈቅድ ለእርሱ የሚናገርለት መብት መኖሩን በፍጥነት እና በማይታበል ዓይነት ሳያስረዳ ሲቀር ስለመሆኑ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 እና 3 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በአንፃሩ የባለሃብትነት መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት የሆነ ሰው ከንብረቱ ላይ መብት ሳይኖረው ከህግ አግባብ ውጭ ንብረቱን በእጁ ባደረገው ሰው ወይም ንብረቱን በያዘው አካል ላይ ክስ በማቅረብ የሚያስመልስበት ህጋዊ መብት (Right to bring Petutary Action) ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1206 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ክስ የሚያቀርብ ሰው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡ ይልቁንም በንብረቱ ላይ በህግ የተቋቋመ የባለሃብትነት መብት ያለው መሆኑን፣ ይህንኑ ንብረቱን ምንም መብት ወይም የተሻለ መብት የሌለው ሰው/አካል/ የወሰደበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡ ሲሆን በዚህ ክሳቸውም በአከራካሪው ይዞታ ላይ የቀደመ የተረጋገጠ በአርሶ አደርነት ይዞታውን የመያዝ መብት እያላቸው አመልካች ይዞታቸውን ነጥቀው በውስጡ የዕቃ ማስቀመጫ ስቶር እና አጥር በመስራት የሁከት ተግባር የፈጠሩባቸው መሆኑን በመጥቀስ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድላቸው፣ለአመልካች የተሰጠው ካርታና የግንባታ ፈቃዱ እንዲመክንላቸው መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተመለከተው አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ በማቅረብ በይዞታው ላይ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው በህጉ አግባብ ሊጠይቁ የሚችሉት ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን በቅድሚያ ሲያረጋግጡ ቢሆንም አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠበትን 90 ካሜ ይዞታ በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ማስረዳታቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

የወረዳው አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ፅ/ቤት በ20/08/2013 ዓም ተጠሪ የልማት ተነሺ አርሶ አደር መሆናቸውንና መንደር 5 ከቶታል ጀርባ የሚገኘው ቦታ <u>ቀደም ሲል</u> በእርሻ እና በግጦሽ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ከመግለፅ ውጪ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙበት ይዞታ በተጠሪ እጅ ሆኖ በእውነት የሚያዙበት ሆኖ በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜ አመልካች ይዞታውን በሀይል በመያዝ በህገወጥ መንገድ አጥር ያተሩበትና መጋዘን የሰሩበት መሆኑን የተረጋገጠበት መሆኑን አያሳይም፡፡ ከዚህ ይልቅ በወረዳው የአርሶ አደር ኮሚቴዎች እና የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ በ08/102013 ዓም የተያዘው ቃለ ጉባኤ ለአመልካች የተሰጣቸው ይዞታ ታጥሮ የሚገኝ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑና በክፍለ ከተማው የመሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያ ግራ ቀኙ በተገኙበት በማጣራቱ ሂደት የያዘው ቃለ ጉባኤ የአመልካች ይዞታ በአመልካች በቆርቆሮ ታጥሮ የተያዘ ይዞታ መሆኑን መግለፁ አከራካሪው ይዞታ በተጠሪ እጅ ያልነበረና ያልተያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡

የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለውን በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታን በተመለከትም አመልካች ለአከራካሪው ይዞታ ከተገቢው የአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የግንባታ ፈቃድ በማግኘት ማከናወናቸው መረጋገጡም ሁለተኛው የህጉ መሰረታዊ መስፈርት ያልተሟላ መሆኑን ያሳያል፡፡

እነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች ደግሞ ከመነሻውም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በሁከት ይወገድልኝ የክርክር ስርዓት ቀርቦ ሊስተናገድ የማይገባው መሆኑን እያሳዩ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ባለይዞታው ማን እንደሆነ መወሰንን የሚጋብዝ መሆኑን እያመለከተ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙ ክርክር ባለሀብትነትን በመፋለም ክስ እልባት ሊያገኝ የሚገባው

መሆኑን በማመልከት የቀረበውን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ ሊያደርገው ሲገባ ይዞታውን የስር 4ኛ ተከሳሽ ለአመልካች ማስተላለፉ የሁከት ተግባር ነው በማለት መወሰኑና ከዚህም በማለፍ በስር 4ኛ ተከሳሽ ላይ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በአመልካች ይዞታ ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ከክርክር አመራር ስነ-ስርዓት አንፃር በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን ግድፈት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.290115 ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 281388 በቀን 20/04/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በሁከት ይወገድልኝ ክስ ክርክር አግባብ ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. ይህ ውሳኔ ተጠሪ በይዞታው ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ በማቅረብ ከማረጋገጥ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 220004
ቀን ፡- ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አህመድ በሽር፡- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ለማ ፈይሳ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ስንሰራ በመተማመን በባንክ ያስገባሁለትን ገንዘብ ብር 700,000.00 እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ገንዘቡ አስቀድሜ ለአመልካች ለሰጠሁት ገንዘብ መልሶ ያስገባልኝ እንጂ የግል ገንዘቡን በመተመማን በባንክ ሂሳብ አላስገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ብር 700,000.00 ተጠሪ

እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ውስጥ ብር 570,000.00 ተጠሪ ከአንድ ቀን በፊት ለአመልካች ለሰጡት ገንዘብ የተመለሰ ስለሆነ ሊከፈል አይገባም፡፡ ቀሪው ብር 130,000.00 በተመለከተ በሕጉ መሠረት የብድር ግንኙነት ያለ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት በከፊል ጉዳዩን ለሥር ወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ወደተጠሪ ግዴታ ጭብጥ ተይዞ ከመመርመሩ በፊት ከሳሽ የሆኑት አመልካች ባቀረቡት ክስ መሠረት የብድር ውል ግንኙነት ከተጠሪ ጋር ያላቸው ስለመሆኑ አለመሆኑ ሊያስረዱ ይገባል፤ ይሕን ጭብጥ መሠረት በማድረግ መርምሮ እንዲወሰን ጉዳዩን ለሥር ወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ ወደሥር ፍርድ ቤት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩ መመለሱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳላገኘ ያሳያል፤ በአዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 26/ለ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ለሰበር ችሎት እንደማይቀርብ ስለተደነገገ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች ጥር 20 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ገንዘብ መቀበሉን አምኖ ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የተከራከረ ስለሆነ ማስረዳቱን የሚጀምረው ተጠሪ ሊሆን ይገባል የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካች የግል ገንዘቡን አላስገባም፣ የነበረበትን ገንዘብ ነው የመለሰው፤ የብድር ዕዳ የለብኝም ብዬም ክጃለሁ፡፡ ጉዳዩ ወደሥር ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ከተወሰነ በኋላ በሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ክሱ ውደቅ ተደርጎ ተወስኗል፤ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ አላቀረበም፡፡ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ስንሰራ በመተማመን በባንክ ያስገባሁለትን ገንዘብ ብር 700,000.00 እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ገንዘቡ አስቀድሜ ለአመልካች ለሰጠሁት ገንዘብ መልሶ ያስገባልኝ እንጂ የግል ገንዘቡን በመተመማን በባንክ ሂሳብ አላስገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ወደተጠሪ ግዴታ ጭብጥ ተይዞ ከመመርመሩ በፊት ከሳሽ የሆኑት አመልካች ባቀረቡት ክስ መሠረት የብድር ውል ግንኙነት ከተጠሪ ጋር ያላቸው ስለመሆኑ አለመሆኑ ሊያስረዱ ይገባል፤ ይሕን ጭብጥ መሠረት በማድረግ መርምሮ እንዲወሰን ጉዳዩን ለሥር ወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ ወደሥር ፍርድ ቤት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩ መመለሱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳላገኘ ያሳያል፤ በአዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 26/ለ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ለሰበር ችሎት እንደማይቀርብ ስለተደነገገ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ሠርዟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ። መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር። ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ። በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ።

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ

2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ክፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ዉሳኔ ሲሆን አቤቱታዉ የቀረበዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም (አንቀጽ 58 ይመለከታል)፣ ጥር 20 ቀን 2014 ዓ/ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ አይደለም ተብሎ ተሰርዟል፤ የሰበር ችሎቱ ውሳኔ አመልካች ጉዳያቸውን በይግባኝና በሰበር የማሳረም ቀጣይ ዕድል ያላቸው መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ውሳኔ ከመሆኑም በላይ በአዋጁ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 391157 ሕዳር 22 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም